# የመኢሶን ሂሳዊ ግምገማ

ሐምሌ 1981

# የመኢሶን ሂሳዊ ግምገማ

## ይዘት

ገጽ

መቅድም....................................................................................1

መግቢያ....................................................................................2

1. መኢሶን....................................................................................4

2. የሂሣዊ ድጋፍ ምንነት....................................................................................8

3. የፖለቲካ መስመርና ድርጊት....................................................................................15
   ሀ. ሕጋዊና ህቡዕ ትግል
   ለ. የትጥቅ ትግል
   ሐ. የሥልጣን ጥያቄ

4. ሌሎች ስህተቶች....................................................................................30
   ሀ. የዴሞክራሲ መብቶች ጥያቄ
   ለ. የሌሎች ዴሞክራሲያዊ አብዮት ሃይሎች ጉዳይ
   ሐ. የውጭ ግንኙነት

5. ከሌሎች ስለሚቀርቡ ሂሶች....................................................................................41
   ሀ. ቀይ ሽብር
   ለ. የደርግ መጠናከር
   ሐ. የሶቭየት ሕብረት መግበት

6. መደምደሚያ....................................................................................62

# መቅድም

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ ስለነበረው ሥፍራና ስለተጫወተው ሚና ሂሣዊ ግምገማ እንዲያደርግ በንቅናቄው የተወሰነው ቀደም ሲል ነው። ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች እስካሁን ሊዘገይ ቻለ። ከዚህ ሂሣዊ ግምገማ ጋር በተያያዘ የንቅናቄውን ሥፍራና ሚና ከኢትዮጵያ ሕዝቦች አጠቃላይ የትግል ሂደት ጋር አገናዝቦ መመርመር ስላስፈለገ፤ ድርጅቱ „መኢሶን በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮት ውስጥ“ በሚል ርዕስት ሰፊ ጥናት አድርጓል።

ይህ ስለመኢሶን ስህተቶችና ጉድለቶች የቀረበው ሂሳዊ ግምገማ በመሠረቱ፤ የጥናቱ ጽሁፍ መደምደሚያ ሆኖ መነበብ ያለበት ነው። ስለሆነም፤ ትኩረታዊ ጥናትን ለማድረግ የሚሻ አንባቢ፤ ተመራማሪ ወይም ማናኛውም የፖለቲካ ሰውና ድርጅት፤ በዚህ ጽሁፍ ላይ ብቻ እንዳይወሰን እናሳስባለን። የተሟላ አስተያየትን ለማግኘት፤ ከላይ የተጠቀሰውን መጽሃፍ ማንበብ አስፈላጊ ነው።

ይህ ሂሳዊ ግምገማ ከመጽሃፉ ተነጥሎ የታተመው በሌላ በምንም ምክንያት ሳይሆን፤ አንባቢ ይሄኛውን ለይቶ ለመመልከትና ለማጤን እንዲ ችል ነው። ወይም ሂሳዊ ግምገማው በመጽሐፉ ቅጠሎች ብዛት እንዳይዋጥ በማሰብ ነው።

በተረፈው ህወሐትና ኢሕአፓ ቀደም ብለው „ግለ-ሂስ“ እንዳደረጉ የሚታወስ ነው። የመኢሶንን ሂሳዊ ግምገማ ከተባሉት ድርጅቶች ጽሁፎችና መግለጫዎች ጋር ማስተያየትና ማነጻጸር ተገቢና ጠቃሚ ይሆናል ብለን እንገምታለን።

## *መግቢያ*

*ሂሳዊ ግምገማ እንዲያው „አድርጌዋለሁ“ ለማለት የሚደረግ መሆን የለበትም። እንደዚሁም፤ ግምገማ በአከላካይ ምክንያቶች ተሸፋፍኖ (ጄስትፋይድ ሆኖ) የሚቀርብ መሆን የለበትም። ሂሳዊ ግምገማ ከሁሉም በላይና በቅድሚያ፤የራ ስን ጉድለቶችና ስህተቶች ለመመርመር የሚደረግ ጥረት ነው። ስለሆነም „ስለራሴ ሂሣዊ ግምገማ አደርጋለሁ“ ብሎ የተነሳ አንድ የፖለቲካ ድርጅት፤ ለጉድለቶችና ለስሕተቶች ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶችንና ሃይሎችን ተጠያቂ በማድረግ ለማምለጥ መሞከር የለበትም። እንደዚህ ዓይነቱ አሰራር፤ ሂሳዊ ግምገማ „አድራጊው“ ድርጅት በመላከክ ጥበብ የተካነ መሆኑን ከማሳየቱ በስረተቀር፤ ይህ ነው የሚባል ትምሕርት እንዲቀሰም የሚረዳ አይሆንም።*

*ይህንን ማለት፤ ጉድለቶችና ስህተቶች ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር መገናዘብ፤ ተለዋዋጭ በሆኑት በየወቅቱ ሁኔታ ውስጥ ተከትተው መመርመር የለባቸውም ማለት አይደለም። አንድ ነጠላ ነገር በራሱ አድራጊ፤ ተደራጊ ተደራጊና አድራጊ ያልሆነውን ያህል፤ አንድ የፖለቲካ ድርጅትም፤ ከአካባቢው ውጭ ተነጥሎ የሚኖርና የሚንቀሳቀስ አይደለም። እራሱን የሚረዳበት ማንነት፤ የሚንቀሳቀስበት ሕብረተሰብ ምንነትና የታሪክ ወቅት፤ ሌሎች የውስጥና የውጭ አጋርና ተቃዋሚ ሃይሎች በአወንታዊና በአሉታዊ የሚወስዷቸውና የማይወስዷቸው የፖለቲካ አቋሞችና እርምጃዎች… ወዘተ ሁሉ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ተጽዕኖ አላቸው።*

*ይህ መሆኑ ግን የነገሮችን ክንዋኔ ለመረዳትና ለማስረዳት ከሚደረግ ጥረት ያለፈ ሥፍራ እንዲሰጠው*

አይገባም። የሂሳዊ ግምገማ ዋና ጉዳይ - ከላይ እንደተባለው የራስን ጉድሎቶችና ስህተቶች መመርመር ነው።

ይህ በዚህ ቢሆን፣ ስህተቶችና ጉድለቶች ሁሉ እኩል ክብደት የላቸውም። ወይም ከብዙዎች መካከል ወሳኞቹ፣ አንዱ ወይም ሁለቱ ናቸው። ይህንን ማለት፣ ሌሎች ስህተቶች አልተፈጸሙም፣ ወይንም ኢምንትና ክብደት የሌላቸው ናቸው፣ ስለሆኑም አይታዩም፣ አይመረመሩም ማለት አይደለም። በተቃራኒው አንዳንዶቹ ከፍተኛ ሌሎቹም አነስተኛ ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ከአቢይ ስህተቱ የሚመነጩና የሚወርዱ ናቸው ማለት ነው። ወይንም ዙሮ ዙሮ፣ ዋነኛ ስህተቱን የሚያጎሉ ናቸው ማለት ነው።

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ፣ ዋና ዋና የሆኑት የንቅናቄው ስህተቶች ላይ እናተኩራለን። ይዘቶቻቸውን እንመረምራለን። ምክንያቶችን እንጠይቃለን። ለመመርመር የምንሻው መስረታዊ ጥያቄ፣ የመኢሶንን የፖለቲካ መስመርና ተግባራዊ አተረጓጎም ነው። እነደዋና ሂስ በሚዘረዘሩት እስተያየቶች ላይ እንመለሳለን።

## 1.መኢሶን

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) በስመ ጥሩው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ተፀንሶ፤ በሐምሌ 1960፤ በምዕራብ ጀርመን፤ ሃመቡርግ በሚባለው ከተማ ተመሠረተ። መስራቾቹ ከተለያዩ ከኢትዮጵያ ብሔረሰቦች የተውጣጡና የማርክሲዝም-ሌኒንዝምን ርዕዩተ-ዓለም የተቀበሉ ምሁራን ነበሩ።

መስራቾቹ ድርጅቱ በተመሰረተበት ጊዜ ስለማርክሲዝም-ሌኒንዝም የነበራቸው ዕውቀት የዳበረና የተሟላ ነበር ለማለት አይቻልም። በተገናዛቢ እየሰለጠኑበት የመጡት በተከተሉት አመቶች ውስጥ በራሱ በመኢሶን ውስጥና በተማሪ ማህበሮች ይከሄዱ በነበሩት ጥናቶችና ከድርጅቱ ተግባራዊ ተሳትፎ ጋር በተያያዘ ነው።

ይሁንና መስራቾቹ ሁሉ ደግሞ፤ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አቢይ ጠላቶች ፊውዳሊዝምና ኢምፔርያሊዝም መሆናቸውን የተረዱ፤ በኢትዮጵያ ጭቆናና ብዝበዛ እንዲጠፋ፤ ዴሞክራሲ፤ ፍትህና እኩልነት እንዲነግሡ፤ የብሔሮች ጭቆና እንዲወገድ፤ አገራቸው እንትበለጽግ፤ ኩራትና ክብርዋ እንዳይገሰሱ ለመታገል የወሰኑ ነበሩ። ለዚህም ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት መቋቋም እንዳለበት አምነው፤ እስከመጨረሻው ድረስ ለመታገል ቆርጠው የተነሱ ነበሩ።

የመኢሶንን መስራቾች በወቅቱ ለትግል ያነሳሳቸው ሀቅ፤ የሃገራቸው ሁኔታና ለሀገራቸው ያላቸው ፍቅር ብቻ አልነበረም። በ1950ዎቹ ዓመታት ውስጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ይካሄዱ የነበሩት የሶስተኛው ዓለም ሕዝቦች የነፃነትና

የጸረ-ኢምፔሪያሊስት ትግሎች ገናናነትም ጭምር አስተዋጽኦ ነበራቸው።

ዘመኑ በአፍሪካ ምድር (ጊኒ ቢሳው፣ ኬፕ ቬርዲ፣ አንጎላ፣ ሞዛምቢክ፣ ዚምባዌ፣ ናሚቢያ) ጸረ-ቅኝ አገዛዝና ጸረ-ዘረኝነት ትግሎች የተፋፋሙበት፣ በእስያ የሕዝባዊት ቻይና የባህል አብዮት እንቅስቃሴና ጸረ-ከላሽነት ትግሎች የተሟሟቁበት፣ የቬትናም የላኦስና የካምፑቺያ ሕዝቦች ጸረ-ኢምፔሪያሊስት የጦር ትግሎች የገነኑበት፣ በሰሜን አሜሪካ የማርቲን ሉተር ኪንግ፣ የጥቁር ግስላዎች (ብላክ ፓንተርስ)፣ የማልኮም ኤክስ፣ የጸረ-ቬትናም ጦርነትና የሴቶች እንቅስቃሴዎች የተነሳሱበት፣ በደቡብ አሜሪካ የኩባ አብዮት፣ የቼ ጌቬራ ትግልና ዝና ትራይ-ኮንትኔታል በሚል የተነሳው የሶስተኛው ዓለም ታጋዮች ንቅናቄ የተስፋፋበት፣ በምዕራብ አውሮፓም ጸረ-ጦርነትና ጸረ-ሥልጣን (አንቲ-ኦቶሪቴሪያን) ትግሎች ያየሉበት ዘመን ነበር።

የነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴዎች ድምር፣ በመኢሶን መስራቾች ላይ ማሕተሙን ያተመ ነበር። ከመስራቾ አባሎቹ መካከል አንዳንዶቹም፣ በያሉበት ሥፍራ ያእንቅስቃሴዎቹ ተሳታፊዎች የነበሩትን ያህል፣ በእንቅ ስቃሴዎቹ አስተያየት ጭምር የታነጹ ነበሩ።

መኢሶን እንደተመሰረተ፣ የንቅናቄው የሃገር ውስጥና የውጭ አካል ክፍሎች ተቋቋሙ። የሥራ ክፍፍል ተደረገ። መኢሶን በዚሁ መሰረት በቅ ድመ-አብዮት ዘመን በአንድ በኩል በሃገር ውስጥ በህቡዕ ተደራጅቶ ሲታገል፣ በሌላው በኩል በውጭ - በተለይም በተማሪ ማህበራት መድረክ አማካይነት ሲንቀሳቀስ ቆየ።

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝቦች በየካቲት 1966 እንአንድ

ሰው ተነሱ። ለዘመናት ሲጨቁናቸው የነበረውን የፊውዳል ሥርዓትና የነጋሲ አገዛዝ ወጥረው በመያዝ፣ መሬት ላራሹ እንዲሆን፣ ዲሞክራሲ እንዲሰፍን፣ ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ፍትሃዊ አስተዳደርና ዳኝነት እንዲረጋገጡ፣ በሃይማኖቶች መካከል የሚደረጉ ልዩነቶች እንዲጠፉ፣ የብሔሮች መብቶች እንዲታወቁ፣ በሥልጣን መባለግ እንዲወገድ... ጠየቁ። ታገሉ።

መኢሶን„ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም"፣ „ሕዝባዊ ኮሚቴዎች ይመስረቱ)፣ „የተራማጆች ሕብረት ይመስረት"፣ „ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይለቀቁ"፣ „መሬት ላራሹ"፣ „ንጉሠ ነገሥቱ ይውረዱ"፣ „የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም" ... የሚሉትን አታጋይና አደራጅ ጥሪዎች በጽሁፎችና በተለያዩ መንገዶች በማስተጋባት ከትግሉ ውስጥ ገባ። እነዚህም መፈክሮች የየካቲት 1966 ሕዝባዊ ትግል እንዲገፋ አስተዋጽኦ ያደረጉ ነበሩ።

የአፄ ሃይለ ሥላሴ መንግሥት መስከረም 2 ቀን 1967 ዕለት ተወገደ። ኢትዮጵያ ከነጋሲ አገዛዝ ተላቀቀች።

ይሁን እንጂ፣ በሰኔ 1966 የተቋቋመው የጦር ሃይሎች አስተባባሪ ኮሚቴ (ደርግ) በዚሁ ዕለት ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ያቋቋመ መሆኑን አውጆ የሥልጣን ባለቤትነቱን አሳወቀ። መኢሶንም በየካቲት መንፈስ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም በመጥራት በደርግ ላይ የሙሉ ተቃውሞ አቋሙን ይዞ መታገል ቀጠለ።

ነገር ግን ደርጉ መውሰድ ከጀመረው አንዳንድ ተራማጅ እርምጃዎችና በተለይም ከየካቲት 1967 የመሬት ላራሹ አዋጅ ጋር በተገናዘበ፣ „ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም" የሚለውን ጥያቄውን አነሳ። በአንጻሩም ሂሳዊ

ድጋፍ ወይም አብዮታዊ ሂስ በሚል የሚታወቀውን የትግል ስልት ቀየሰ።

## 2. የሂሳዊ ድጋፍ ምንነት

ሂሳዊ ድጋፍ የኢትዮጵያ አብዮት በወቅቱ ይገኝ ከነበረበት ሁኔታ የመነጨ የመኢሶን የፖለቲካ መስመር ነው። እንደዚሁም መስከረም 2 ቀን 1967 ሥልጣንን በጨበጠው ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የመደብ ባህርይና ይኸው መንግሥት በወሰዳቸው የፖለቲካ እርምጃዎች ሚዛን ላይ ተመስርቶ የተቀየሰ መስመር ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለዘመናት ተጭኖባቸው ሲጨቁናቸውና ሲበዘብዛቸው በኖረው ሥርዓት ላይ ከጠረፍ ጠረፍ አሻፈረን አንገዛም ብለው ቢነሱም፣ የተነሱት በግብታዊነት ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉንም ለውጥ ፈላጊ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚወክልና የራሳቸው የሆነውን አብዮታቸውን መርቶ የሥልጣን ባለቤት ሊያደርጋቸው የሚያበቃ ድርጅት አልነበራቸውም። በዚህም ምክንያት የግብታዊ እንቅስቃሴ አንዱ አካል የነበረውና የታጠቀው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች አስተባባሪ ኮሚቴ (ደርግ)፣ እየፈራና እየቸረ፣ በጊዜያዊነት ስም እየማለና እየተገዘተ ሥልጣንን ጨበጠ።

ደርጉ በሕዝብ ግፊት ንጉሡን ከሥልጣን ካወረደና ሥልጣንን ከጨበጠ ከመስከረም 2 ቀን እስከ የካቲት 25 ቀን 1967 ባለው ጊዜ ውስጥ በወሰዳቸው ልዩ ልዩ እርምጃዎች የወላዋይነትና የፀረ-ዴሞክራሲያዊነት ባሕሪዎች ቢታዩበትም በአመዛኙ ሕዝባዊና ወሳኝ ፀረ-ፊውዳል እርምጃዎች መካከል፣ የየካቲት 25 ቀን 1967 የገጠር መሬት አዋጅና የእድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ይገኙባቸዋል።

ሂሰዊ ድጋፍ የሚባለው የመኢሶን የፖለቲካ የትግል ስልት የተቀየሰው፣ መኢሶን የወቅቱን የቅራኔዎች

አቀማመጥና የመደቦች አሰላለፍ በሚመለከት ካደረገው ግምገማ በተገናዘበ ነው። መኢሶን፣ በተለይም በየካቲት የገጠር አዋጅ ምክንያት፣ የወቅቱ አቢይ ትግልና ትንቅንቅ በኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች በአንድ በኩልና በቀድሞ ገዥ መደቦች ባለመሬቶሎች በሌላው በኩል መካከል መሆኑን ተመለከተ። በዚህ አሰላለፍ ውስጥ ደርጉ፣ ባመዛኝ ጸረ-ፊዳል ሃይል መሆኑን አጤነ። ስለሆነም፣ ከደረጉ ጋር ጊዜያዊ ትብብርን ማድረግ እንደሚገባ ወሰነ።

የሂሳዊ ድጋፍ መስመር ዋና ዓለማ፣ በወቅቱ በአመዛኝ ተከስቶ የነበረውን አብዮታዊ ሁኔታ ተጠቅሞ፣ አብዮቱ የጎደለውን ህሊናዊ ሁኔታ (በተለይ የንቃተ ሕሊናና የድርጅት) በማሟላት፣ የኢትዮጵያን ሕዝቦች በነቃ፣ በተደራጀና በታጠቀ ትግል ለሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሥልጣን ባለቤትነት ማብቃት ነበር። ይህንኑም፣ „የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ዋና ቅራኔ“ በሚል ርዕስ ሥር በታሕሳስ 6 ቀን 1968 የወጣው የሰፊው ሕዝብ ድምፅ እትም ቁጥር 33፣ „አብዮታዊ ሂስ (ሂሳዊ ድጋፍ) ስንል ምን ማለታችን ነው?“ ብሎ በመጠየቅ እንደሚከተለው አትቶበት ይነበባል፦

> *„ዋናው መነሻችን የመንግሥት ሥልጣን በሚያስተማምን አኳሁዋን ወደሰፊው ሕዝብ እጅ የሚገባበትን መንገድ መሻት ነው። ለዚህም እስከመጨረሻው እንታገላለን። ስለዚሕም ይህን ደርግ በጸረ-ህዝብነቱ፣ በጸረ-ዲሞክራሲያውነቱ፣ በጸረ-አብዮትነቱ እንቃወመዋለን፣ እንታገለዋለን። ሠፊው ሕዝብ ተደራጅቶና ታጥቆ ከደርጉም ሆነ እርሱን ከሚተካው ሌላ ተመሳሳይ መንግሥት እጅ ሥልጣን ፈልቅቆ እንዲወስድ የሚያስችለውን ትምሕርት እንዲያገኝ፣ እንዲደራጅ አስፈላጊውን ትግል እናደርጋለን።*
>
> *ዋናው አብዮታዊ ቁም ነገር የአብዮቱ ወደፊት መገፋት፣ ሥልጣን ወደተደራጀ ሰፊ ሕዝብ እጅ መግባት ስለሆነ፣ ግንባር ቀድሙና ሃቀኛው ተራማጅ በጠቅላላውም*

ሰፊው ሕዝብ እየታገለ እንዲደራጅ፣ እየተደራጀም እንዲታገል እንታገላለን እንጂ፣ ያለምንም ዝግጅት በሥልጣን ዝውውር ላይ ብቻ በማተኮር በጓዳ ሾልከው የሚገቡ ቀልባሾች ለፀረ-አብዮት ሃይሎች መሳሪያ እንሆንም። ከሰፊው ሕዝብ ዋና ጠላቶች ጋር አንተባበርም። የአብዮት አንጻር እያየን ጸረ-አብዮት ሃይሎችን በየደረጃው እየለየን እንታገላቸዋለን።

የተለያዩ ጠላቶችን በየደረጃው እየለየን እንታገለቸዋለን እንጂ፣ ሁለት እግር ሰላለን ሁለት ዛፍ ላይ እወጣለሁ የሚለውን የታክቲክ ስህተት በማድረግ ሁለት ጦርነት በአንድ ጊዜ አናውጅም።

ለአብዮቱ መግፋት ስንል የሁለተኛ ደረጃ ጠላቶችን በልዩ ልዩ ዘዴ እናዳክማቸዋለን እንጂ፣ ከዋናው ጠላት ጋር እንዲሰለፉ አናደርግም፣ ወይም ከዋነኛው ጠላት ጋር ተሰልፈን በሁለተኛ ደረጃ ጠላቶች ላይ አን ዘምትም።

በመሆኑም፤ ሂሣዊ ድጋፍ ማለት፤ በወቅቱ በተገኙት ሕጋዊ መስኮች እስከመጨረሻው መጠቀም፤ ለሌሎች ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ እርምጃዎች ሳይታክቱ መታገል፤ የሕዝቡን ጥያቄዎች ማስተጋባት፤ የደርጉን ጸረ-ሕዝብና ፀረ-ዲሞክራሲያዊ እርምጃዎች ማጋለጥና መታገል ማለት ነው።

ሂሳዊ ድጋፍ ማለት፤ ደርጉ ለሕዝባዊ ለውጥ ያለውን ችሎታና ፍላጎት እስኪያሟጥጥ ድረስ ተባብሮ ፊውዳሊዝምን መደምሰስ፤ ማለት ነው። ባጭሩ፤ በወቅቱ ሥልጣንን የጨበጠው መንግሥት ለአንዲት ተጨማሪ ዕለት እንኳን በሕዝብ ወገን እስከቆመ ድረስ፤ አብሮ ተሰልፎ ፀረ-ሕዝብ ሃይሎችን መታገል የወደፊቱን የሕዝባዊ ሥልጣን መሠረት ማዳበር ማለት ነው።

ድጋፍና ትብብርም ሲባል፤ በደፈናው ድጋፍ፤ በደፈናው ትብብር ማለት አልነበረም። ደርጉ አንዳንድ ሕዝባዊ

እርምጃዎችን ቢወስድም፤ አብዮቱን ከግቡ እንደማያደርሰው ሳይታክቱ መግለጽና ማሳየት ማለት ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝቦችም ይህንኑ ተገንዝበው፤ ንቃት ድርጅትና ትጥቃቸውን እንዲያጠናክሩ ማድረግ ማለት ነበር። „መኢሶን በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮት ውስጥ“ በሚል ርዕስ የወጣው የሰፊው ሕዝብ ድምፅ እትም ቁጥር 50 (ጥር 30 ቀን 1969) ይህንኑ ለምሳሌ እንደሚከተለው ያስቀምጠዋል፦

> „የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽና ገዜያዊ ወታደራዊ አሰተዳደር ለአብዮቱ እስካሁን ያደረጉት አስተ ዋጽኦ በጣም ከፍተኛ መሆኑንና ወደፊትም ብዙ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ ቢያምንም፤ እነዚህ ሃይ ሎች እንዳሉ እስከመጨራሻው ለአብዮቱ ይቆ ማሉ በሚለው የህልም እንጀራ ድርጅታችን ፈጽሞ አያምንበትም።
>
> „በደረጉ ውስጥም ሆነ በመለዮ ለባሹ ውስጥ የሉት አበዮታዊና ፀረ-አብዮታዊ ሃይሎች ሰልፋቸውን ለይ ተው የሚፋጠጡበት ወቅት በርግጥ ይመጣል። ለዚ ህም ነው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በየዕለቱ ይበልጥ መንቃት፤ መደራጀት፤ መታጠቅ ያለበት።

የመኢሶን ሂሰዊ ድጋፍ መስመር፤ ሂስንና ድጋፍን እንደሁኔታው በማፈራረቅ፤ ሕጋዊና ሕቡዕ የትግል ስልተሎችን አጣምሮ በሥራ ላይ በማዋል በዚህም መሠረት ከነበረው ደርግ ጋር ጊዜያዊ ትብብር በመፍጠር፤ በመሰረታዊ ጠላቶች ላይ በጋራ ለመዝመት የሚያስችል የትግል ስልት ነው። ብሎም በዚህ ሂደት ውስጥ፤ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝቦች በነቃ በተደራጀና በታጠቀ አመጻቸው፤ ሥልጣንን ለመጨበጥ እንዲበቁ ለማድረግ የትግል መስመር ነው።

በዚህም መንፈስ መኢሶን ከየካቲት 1966 እስከ የካቲት

1967 ያራመደውን፤ „ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም“ ይል የነበረውን የሙሉ ተቃውሞ መስመሩን አነሳ። ሒሳዊ ድጋፍ በሚለው መስመሩ ተካው። መኢሶን ይህንን የትግል ስልት ሊቀይስ የቻለው፤ የድርጅቱን ህሊናዊነት ( ሰብጀክቲቭዝም) በመታገልና ከላይ እንደተባለው የሃገሪቱን የቅራኔዎች አፈረጃጀትና የሃይሎችን አሰላለፍ በማጤን ነው።

በወቅቱ እሕአፓም ሆነ የብሔር ድርጅቶች ወይንም የኤርትራ ግንባሮች በኢትዮጵያ እንደዚያ የጦፈ የአብዮትና ፀረ-አብዮት ትንቅንቅ እየተካሄደ ቢሆንም፤ አንዴ „አብዮት የለም“ ሌላ ጊዜ „ፋሺዝም ነገሠ“ አሁንም ሌላ ጊዜ ደግሞ „መስከረም 2 ዕለት አብዮቱ አቆመ“ እስከማለት ደርሰው ነበር።

ዛሬ ከ15 ዓመታት በሁዋላ፤ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት የፈነዳ ብቻ ሳይሆን፤ ለተወሰኑ ዓመቶች አብዮታዊ ትግሎች እንደተካሄዱና የኢትዮጵያ ሕዝቦች በወቅቱ አቢይ ድሎችን ተጎናጽፈው እንደነበር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማያምኑና የማይቀበሉ ጥቂቶች ናቸው። ሂሳዊ ድጋፍ አንድም የመነጨው፤ አብዮት በመካሔድ ላይ መሆኑን መኢሶን በወቅቱ እንደሃቅ ስለተቀበለው ነው።

ይሁንና እንደታሪክ ሃቅ ደግሞ፤ መኢሶን ደርጉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ከደርጉ ጋር የተባበረ ድርጅት አለመሆኑ እንዲያዝ ያስፈልጋል። የመ ኢሶን ሒሳዊ ድጋፍ መስመር በአብዮቱ ዘመን በሥራ ላይ የዋለው በሁለት ወቅቶች፤ በሁለት ዓይነትና ደረጃዎች ነው።

የጀመሪያው ወቅት፤ ከየካቲት 1967 እስከ ሚያዝያ 1968 ያለው ነው። በዚህ ወቅት መኢሶን ከደርጉ ጋር ቀጥተኛ ትብብር ሳይመሰርት፤ በተለይ የገጠር መሬት

አዋጅ በሥራ ለመተርጎም በሚደረገው ትግል ውስጥ በሙሉ ሃይሉ ተሳተፈ። ለዚህም በርካታ አባሎቹንና ደጋፊዎቹን በመሬት ይዞታና በአገር አስተዳደር ሚኒስትሮችና በእድገት በህብረት  የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ጣቢያዎች ውስጥ በማሰማራት ታግሏል።

ሁለተኛው ወቅት፤ ከሚያዝያ 1968 እስከ ነሃሴ 1969 የነበረው - የ15 ወሮች ጊዜ ነው። ይሂኛው መኢሶን በሚያዝያ 13 ቀን 1968 በወጣው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መሠረት፤ ከደርጉ ጋር ጊዜያዊ ትብብርን መስርቶ የታገለበት ወቅት ነው። ደርጉ ይህንኑ የትብብር መድረክ እየሻረና እየከዳ በአመዛኙ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ እየሆነ በወጣበት ጊዜና የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝቦች ጥቅምና ፍላጎት ለማራመድ እንቅፋት በሆነበት ጊዜ፤ መኢሶን ጊዜያዊ ትብብሩን አቋረጠ። ይህንንም በነሃሴ 14 ቀን 1969 ባደረገው የትግል ስልት ለውጥ እርምጃ በይፋ አሳወቀ።

ሂሳዊ ድጋፍ በወቅቱ ከነበሩት የቅራኔዎች አፈረጃጀትና የአብዮት ወዳጅና ጠላት ሃይሎች አሰላለፍ አንጻር፤ ትክክለኛ የትግል ስልት ነበር። መኢሶን በዚህ የትግል ስልት መሰረት ባደረገው ተሳትፎ በአብዮቱ ለተገኙት ድሎች አስተዋጽኦ አድርጓል። በኢትዮጵያ የፊውዳሊዝም ሥርዓተ-ማህበር መደምሰስ ዋነኛ ድል ነው።

ይሁን እንጂ፤ በአማካይ ከጥር/የካቲት 1969 ጀምሮ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ደረጃ በደረጃ ተቀለበሰ። በርካታ የሕዝብ ድሎች ተነጠቁ። የመንግሥቱ ሃይለማርያምና የግብረ አበሮቹ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ሰፈነ።

የኢትዮጵያ አብዮት በርካታ ድሎችን ከተጎናጸፈ በሁዋላ፤ በሂደት ላይ እንዳለ በተደራረቡ ምክንያቶች ደረጃ

በደረጃ የተቀለበሰ አብዮት ነው። የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝቦችም ድሎቻቸውን ላለመነጠቅ መራራ ትግሎችን አካሂደዋል። በዚሕ ትንቅንቅ ውስጥ፤ ወታደራዊው አምባገነን መንግሥት ያወረደባቸውን አረመኔያዊ ግፍና ጭፍጨፋ፤ አገራችን በታሪኳ አይታው አታውቅም። መኢሶንም ከአብዮቱ መቀልበስ ጋር አብሮ ተመታ። ከፍተኛ ጥቃትም ደረሰበት።

## 3. የፖለቲካ መስመርና ድርጊት

### ሀ. ሕጋዊና ሕቡዕ ትግል

ሂሳዊ ድጋፍ በሰፊው በተከፈቱት ሕጋዊ መስኮች እሰከመጨረሻው ድረስ መጠቀም ማለት ብቻ አልነበረም። በሌላ ገጽታው፣ በአንድ በኩል የድርጅቱን ነጻ ህልውና መጠበቅ፣ በሌላው በኩል፣ መኢሶን በትንቅንቅ ሂደት ውስጥ „የአብዮትና የፀረ-አብዮት ሃይሎች ሰልፋቸውን ለይተው የሚፋጠጡበት ወቅት በርግጥ ይመጣል“ ላለው ወቅት፣ በተለይ በህቡዕ መንገዶች የድርጅትና የራስን የትጥቅ ሃይል ማዘጋጀትና ለሚቀጥለው ትግል መብቃት ማለት ነበር።

መኢሶን የተከፈቱትን ህጋዊ መስኮች እስከመጨረሻው ድረስ ተጠቀመባቸው። አባላቱንና ወዳጆቹን በህጋዊ መስኮች አሰማርቶ ባካሄደው ትግል፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ፀረ-ፊውዳል ትግል እንዲጠናከርና እንዲገፋ አገዘ። የገበሬ የወዝአደር፣ የከተማ ኗሪዎች፣ የወጣቶችና የሴቶች ማህበሮች የንቃት፣ የድረጅትና - እስከተወሰነ ደረጃም ድረስ የትጥቅ ሃይላቸው እንዲዳብር በሰፊው ሰራ። ታገለ። መኢሶን በዚህ ተሳትፎው በኢትዮጵያ ፊውዳሊዝም እንዲደመሰስና አብዮቱ እንዲራመድ ያደረገው አስተዋጽኦ አዎንታዊ ነው።

ይሁን እንጂ፣ መኢሶን በዚሁ ትግል ውስጥ ሌላውን - ማለትም፣ በሕቡዕ የድርጅትና የትጥቅ ሃይል ማደራጀት ገጽታ፣ በውል በተግባር ሳይተረጉመው ቀረ። ይህም ዙሮ ዙሮ በአንድ በኩል፣ የሂሳዊ ድጋፍ መስመር በሚጠይቀው መሠረት ንቅናቄውን በአንዳንድ ዋና ጥያቄዎች ላይ ነጻና

ግልጽ አቋሞችን ከመግለጽና ከማስተጋባት እንዲታቀብ ያደረገው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፤ ደርጉን ተቃርኖ መቀጠል ለሚገባው የአመጽ ትግል መደረግ የነበረበትን አስፈላጊ ዝግጅት ያላሸቀ ጉዳይ ጭምር ነው።

መኢሶን ከአባላቱና ከወዳጆቹ መካከል እጅግ ብዙዎቹንና ዋና ዋና መሪዎች ሳይቀሩ፤ በህጋዊ የትግል መስኮች ላይ እንዲሰማሩ አደረገ። ይህ አሰራሩ፤ የህቡዕ አካሉን የሰው ሃይል ያሚጠጠና ሕገ-ወጡን ዝግጅት የበደለ አሰራር ብቻ አልነበረም። እዚያው በዚያው የድርጅቱን ገበና ያጋለጠና የመጨረሻ መጨረሻም፤ የድርጅቱን ነጻ ህልውና በአስጊ ሁኔታ ላይ የጣለ ነው።

ከአመራሩ ጀምሮ ያሉት የንቅናቄው አባሎች በዕለት ተዕለቱ የሕጋዊ መስኮች ትግል የተወጡትን ያህል፤ ድርጅቱ በአንድ በኩል አጠቃላዩን የጉዞ አቅጣጫ ቆም ብሎ ማየት ተሳነው። በሌላው በኩል፤ ለድርጅቱ ቀጣይ ትግል የሚያገለግሉትን የማፈግፈጊያና የመከላከያ አምባዎች የመገንባትና የማደ ረጀት ጉዳዮች ትኩረት ሳይሰጣቸው ቀረ። በአብዮቱ ሂደት ውስጥ ከጥር/የካቲት 1969 ጀምሮ ዋናው ትንቅንቅ በመኢሶን በአንድ ወገንና በደረግ (ሰደድ) በሌላው ወገን ሆኖ በመጣም ጊዜ፤ መኢሶን ነጻ አቋሙን መጠበቅና ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን፤ ራሱን ለመከላከል የተሳነው ድርጅት ሆኖ ተገኘ።

በህጋዊ የትግል መስክ ተሰማርተው የነበሩት አባሎቹና ወዳጆቹ በግልጽ የታወቁ ስለነበሩ፤ በደርጉ የፀጥታ ሃይሎች በቀላሉ ተለቀሙ። ድርጅቱም ሊጋለጥና በቀላሉ ሊመታ ቻለ። መኢሶን ታዋቂ መሪዎቹን አጣ። ጥቂት የማይባሉ አባሎቹና ወዳጆቹ ተያዙ፤ ታሰሩ፤ ተጉላሉ ተገደሉ፤ ሌሎቹም ተሰደዱ።

መኢሶን በሌላው ወገን፣ ነጻ አቋሙን በይፋ አጣርቶና ለይቶ ያለመግለጹን ያህል፣ በድርጅቱና በደርግ (ሰደድ) መካከል የአቋም የአመለካከትና የድርጊት ልዩነቶች እንዲደበዝዙ ሆነ። ለዚህም እስከዛሬ እንደመኢሶን አድራጎቶች ተደርገው የሚነገሩ፣ ነገር ግን መኢሶን በወቅቱ ይፋ አቋም ሊወስድባቸውና ሊታለፉም የማይገባቸው የነበሩ ሁለት ጉዳዮችን መጥቀስ ተገቢ ነው። አንደኛው ግርማ ከበደ የተባለው ሰው በመጋቢት 1969 የፈጸመው አሰቃቂ ግድያ ጉዳይ ነው። ሌላው በሚያዝያ 22 ቀን 1969 በአዲስ አበባ ከተማ ቁጥራቸው በርካታ በሆነ ወጣቶች ላይ የተፈጸመው ግድያ ነው።

ከመጋቢት 14 እስከ መጋቢት 18 ቀን 1969 „የመንጥር ዘመቻ" የተባለው የአሰሳና የትጥቅ ማስፈታት እንቅስቃሴ በአዲስ አበባ በተካሄደበት ጊዜ፣ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አካባቢ የቀበሌ 07 ሊቀ-መንበር የነበረው ግርማ ከበደና አበሮቹ፣ ዘጠኝ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኞችን አረመኔያዊ በሆነ መንገድ ገደሉ። ጓደኞቹ እንደሚታወሰው ሕዝብ በተሰበሰበበት መጋቢት 24 ቀን 1969 በአደባባይ ተረሸነዋል።

የግርማ ከበደን አሰቃቂ ግድያ አንተርሰው፣ ኢሕአፓና ቢሮክራሲው በመኢሶን ላይ ተረባረቡ። አንዳንዶቹ፣ „ግርማ ከበደ የመኢሶን አባል ነው" እያሉ በእርግጠኝነት አወሩ። ሌሎቹ „ግርማ ከበደ ግድያውን የፈጸመው በመ ኢሶን ትዕዛዝ ነው" እያሉ፣ በመኢሶን ላይ ዘመቱ። እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ምክንያትና ፍላጎት ነበራቸው።

ሃቁ ግን፣ ግርማ ከበደ መቼም ቢሆን የመኢሶን አባል ሆኖ አያውቅም። የዚህን ሰው መታጠቅ በሚመለከተው፣ መኢሶን እንዲያውም በተጻራሪው፣ ግርማ

ከበደ የቦዘኔ ባህርይ የሚታይበት አደገኛ ግለሰብ መሆኑን በማስገንዘብ፤ ግርማ ከበደ በግል እንዳይታጠቅ አስተያየቱን ለሚመለከተው ክፍል ሰጥቶ ነበር። ይሁንና በተለይ ለገሰ አስፋው ይህንን የመኢሶንን አስተያየት በመቃረን ግርማ ከበደን ለግሉ ክላንሽኮፍ አስታጠቀው። ክላንሽኮፍ ማስታጠቅ በወቅቱ <u>ለየትኛውም</u> የቀበሌ ማሕበር መሪ የተደረገ አልነበረም።

በዚህ የአብዮታዊ ሰደድና የለገሰ አስፋው ድጋፍ የልብ ልብ የተሰማውና የተማመነው ግርማ ከበደ፤ ከግብር አበሮቹ ጋር ሆኖ በግሉ የሞት ብያኔ እየሰጠ በማንአለብኝነት ግድያዎችን ፈጸመ።

መኢሶን ይህንን ሃቅ በወቅቱ ለሕዝብ ይፋ ማድረግ በተገባው ነበር። የሁንና፤ በዚህ ዩዳይ ያ ሁሉ ዘመቻ ሲካሄድበት ምንም ዓይነት መግልጫ ሳይሰጥበት ቀረ። ይህም ከባድ የፖለቲካ ስህተት ነው።

በዚያን ወቅት በርካታ የንቅናቄው አባሎችና ወዳጆች መግለጫ እንዲሰጥበት አበክረው ቢጠይቁም፤ የድርጅቱ አመራር በወቅቱ በአንድ በኩል ንቅናቄው በመጋቢት 1969 ባደረገው ኮንፈረንስ ውሳኔ መሰረት፤ ለትግል ስልት ለውጥ አጣዳፊ ዝግጅቶችን የሚያደርግበት ወቅት መሆኑን በማስመልከትና፤ በሌላውም በኩል፤ ድርጅቱ የሰደድን ምላሽ ለመቋቋም በማይችልበት ሁኔታ ይፋ ግጭትን በመጋበዝ ድርጅቱን ማስመታት ይሆናል በማለት፤ ጥያቄዎቹን ሳይቀበል ቀረ። ይህም ስህተት ዞሮ ዞሮ የሚያሳየው መኢሶን ነጻ አቋሙን ለመግለጽ የማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ተገኝቶ እንደነበር ነው።

በተፈጠረው አጋጣሚ ተጠቅሞ በተለይ የኢሕአፓ አመራር መኢሶንን በግርማ ከበደ ወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ ባካሄደው ቅስቀሳና፤ መኢሶንም እንደተባለው በወቅቱ ምንም ዓይነት መግለጫ ባለመስጠቱ ምክንያት፤ ሰዎች ግርማ ከበደን

እንደ መኢሶን አባል ማየታቸው አያስገርምም።

በተረፈውና ከታሪክ ግንዛቤ አንጻር ደግሞ፤ የወታደራዊው ሰደድ መንግሥት „ቀይ ሽብር“ መኢሶን የትግል ስልት ለውጥ ካደረገ ከወራት በሁዋላ በ1970 ዓ.ም. በሰፊው በተፈጸመበት ጊዜ፤ የመጋቢት 1969 አንድ ግርማ ከበደ በመቶ የሚቆጥሩ ግርማ ከበደዎች ሆኖ እንደተወለደና እንደተራባ ማስተዋሉ አስፈላጊ ነው። እነዚህን በመቶ የሚቆጠሩ ግርማ ከበደዎች የፈጠሩና በሕዝብ ላይ ለእልቂት ተልእኮ ያሰማሩ፤ እነመንግሥቱ ሃይለማርያም፤ ለገሠ አስፋው፤ ሻለቃ ብርሃኑ ከበደና ተባባሪዎቻቸው የወዝ አደር ሊግና መሌሪድ ነበሩ። በዚህም ዘመን፤ የነዚሕኞቹ ግርማ ከበደዎች የፍጅት ግድያ ዘመቻ ከወረደባቸው ክፍሎች መካከል አንደኛው፤ መኢሶን ራሱ ነው።

ሁለተኛው ጉዳይ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው፤ በሜይ ዴይ ዋዜማ - ሚያዝያ 22 ቀን 1969 የደረሰውን ሁኔታ ይመለከታል። በዚህም ዕለት ቁጥራቸው እስከ 300 የሚገመት ወጣቶች በአዲስ አበባ ከተማ አለቁ። ይህም መኢሶንን የደርጉ ተባባሪ በማድረግ ጭምር ብዙ ብዙ የተጻፈበትና የተነገረበት ጉዳይ ነው።

መኢሶን በዚህም ጉዳይ ላይ በወቅቱ መግለጫ ሳይአጥበት ቀርቷል። የወቅቱ ምክንያት፤ ከላይ ስለግርማ ከበደ ከተሰጠው ምክንያትና ሁኔታ የተለየ አልነበረም። የሁንና መኢሶን እስከሚያውቀው ድረስ፤ በሚያዝያ 22 ቀን 1969 የደረሰው ምንድን ነበር?

ሚያዝያ 22 ቀን 1969፤ ማለትም ሜይ ዴይ (የሰራተኞች ቀን) የሚወልበት ዋዜማ ነው። በዚህ ዕለት - የወዝአደሩ፤ የአዲስ አበባ አካባቢ ገበሬዎች፤ የቀበሌ ማሕበሮች፤ የመንግሥት ሰራተኞች፤ መለዮ ለባሾች

ወዘተ ... ሁሉ ያተኮሩት በማግሥቱ ስለሚከበረው በዓል በሚደረገው ዝግጅት ላይ ነበር። መኢሶንና ሌሎች የሕዝብ ድረጅት ፅ/ቤት አባሎችና ሰራተኞችም እንደዚሁ ለዚሁ በዓል መሰናዶ እያደረጉ ነበር።

በዚህ የሜይ ዴይ በዓል ዋዜማ ዕለት፤ የኢሕአፓ „ልዩ ዝግጅትስ“ ምን ነበር?

ወደምሽቱ ላይ ኢሕአወሊ ይባል በነበረው የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ እየተመሩ በርካታ የወጣት ሰልፎች ብዙ የአዲስ አበባ ቀበሌዎችን በድንገት አጥለቀለቁ። ሰልፈኞቹ ግን እንደሚነገርላቸው፤ ከቶም ሰላማዊ አልነበሩም። ከተሰላፊዎቹ መካከል በአንጋችነት የታጠቁ የኢሕአፓ ስኳድ አባሎች ነበሩ። እነዚህም ከሰልፈኞቹ መካከል ሆነው በቀበሌ ጽ/ቤቶች ላይ ሽጉጥ በመተኮስ፤ የእጅ ቦምቦችን በመጣልና የሞሎቶፍ ኮክቴል በመወርወር ቀበሌዎችን ማጥቃት ጀመሩ።

በዚህም ጊዜ፤ በድንገት በወረራቸው የወጣቶች ሰልፍ ብቻ ሳይሆን፤ በተከፈተባቸው ጥቃት ይበልጡን የተደናገጡት የቀበሌ አብዮት ጥበቃ አባሎች በአጸፋው በሰጡት የተኩስ ምላሽ፤ ብዙ ወጣቶች ሞቱ። ሌላም፤ ያልታጠቁ ቀበሌዎች ደርግ ጸ/ቤት እየደወሉ በጠየቁት እርዳታ መሰረት የተሰማራው የደርጉ ዘመቻ መምሪያ ሃይል፤ እንደዚሁ ቁጥራቸው ከፍ ያለ ወጣጦችን ፈጀ። ከዚህም በተጨማሪ በቦሌ መንገድ አካባቢ ከተሰላፊዎቹ በአንዱ ወጣት ተይዞ የነበረው ቦምብ አጠቃቀሙን ባለማወቅ በተሰላፊዎቹ መሃል በመፈነዳቱ ምክንያት የጥቂት ወጣቶች ህይወት አለፈ።

ይሁንና እንግዲህ፤ ሰልፉ በማን ተጠራ? በማን ተዘጋጀ? እንዴትስ ተካሄደ? ለምን በዚያ ዕለት በየቦታው ተደረገ? የሰልፉስ ዓለማ ምን ነበር?

ሰልፉን የጠራው የኢሕአፓ አመራር ነበር። አዘጋጁና አስፈጻሚውም የወጣት ክንፉ ኢሕአወሊ ነበር። ሆኖም በሚያዝያ 22 ዕለት ተዘርግፎ የወጣው አብዛኛው ወጣት የሰልፉን ግብና ከበስተጀርባው የተጠነሰሰውን እቅድ ይወቅ አይወቅ በርግጠኝነት ለመናገር አይቻልም።

የኢሕአፓ አመራር ግን፣ ግልጽ ፍላጎትና ግብ ነበረው። ለዚህም፣ በራሱ በኢሕአወሊ በወቅቱ የተበተኑ ወረቀቶች እንቅስቃሴውን „የሜይ ዴይ አመጽ“ (ኢንሰሬክሽን)“ እያሉ „ታሪካዊ ስፍራ“ ለመስጠት እንደሞከሩ ለማስታወስ ይቻላል።

ይህን የመሰለ በወጣቶች ላይ የተመሰረተ አመጽ እንደልዩ ወቅታዊ የትግል ስልትና ከፖለቲካዊውና ከድርጅታዊ ተግባሮች ቅድሚያ ተሰትቶት በኢሕአፓ የወጣት ክንፍ (ኢሕአወሊ) በተጨማሪ እንደተወሰደ የሚያሳየው፣ በዚያን ወቅት በልሳኑ በአብዮታዊ ወጣት፣ ቁጥር 9 እትም ላይ (አሁንም እንደተለመደው ቀን ያልተጻፈበት) „ያለንበት ሁኔታና የወቅቱ ተግባራችን“ በሚል ርዕስ ለወጣቶች የሚከተለውን መመሪያ መስጠቱ ነበር።

> „ ... ጭቁኖች ለጸረ-ሕዝብ አመጽ፣ አብዮታዊ አመፅ ምላሽ እየሰጡ ናቸው። ነጭ ሽብርን በቀይ ሽብር እየመከቱ ናቸው። ጸረ-ሕዝቦችን በከተማም በገጠርም እያ ሳደዱና እየደፉ ናቸው።
>
> ... የአብዮታዊ ወጣቶች ተግባራችን ምንድነው? ለተጀመረው የአመጽ ትግል ልዩ ዝግጅት ማድረግ አለ ብን። የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሳዊና ቴክኒካዊ ፍላጎቶች በራሳችን አነሳሽነት ማሟላት አለብን። (ስርዝ የተጨመረ)

የኢሕአፓ አመራር እንደወትሮው፣ በዚሁ ዕለት ሕዝብን

በወጣቶች ተክቶ „ዓመጽን“ ለመጫር በጀብደኝነት ተነሳ። በወቅቱ እንደተገመተው ሚያዝያ 22 ቀን 1969 ዕለት ሁለት ሰዓት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ሕይወታቸው ያለፈው ወጣቶች ቁጥር ከ300 የማያንስ ነበር።

ይህ ሀቅ ነው እንግዲህ፣ በኢሕአፓ አመራርና በአንዳንድ የውጭ ጋዜጠኞች በመኢሶን ላይ እየተላከከ የሚነገረው። መኢሶን ከዚህ በላይ ያቀረበው የታሪክ ሀቅ፣ ወደፊት በራሳቸው የኢሕአፓ አባል በነበሩ ሰዎች ይበልጥ እንደሚነገር ይተማመናል።

ወታደሮችም ሆኑ የቀበሌ አብዮት ጥበቃ አባሎች የወሰዱት ያልተ መጣጠነ የአጸፋ እርምጃ በማያሻማ የሚወገዝና መወገዝም ያለበት ነው። በዚሁ ዕለት በተጨማሪም ደግሞ፣ አንዳንድ የቀበሌ መሪዎች በአንዳንድ ሆስፒታሎችና በተለይም በምኒልክ ሆስፒታል አካባቢ፣ ወላጆች የልጆቻቸውን አሬሳ ሲጠይቁ „ሬሳ የምትወስዱት የጥይት ዋጋ ከፍላችሁ ነው“፣ እያሉ ጠይቀዋል።

ይህም የሚወገዝ ሲሆን፣ በሌላው ወገን፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ለጥይት መግዣ ሬሳ ይሸጥ ነበር “እያሉ በኢትዮጵያውያን ማንነት ላይ መዝመት ግን ነገሮችን ማጋነን ብቻ አይደለም። ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያን ለዓለም ሕበረተሰብ አረመኔ አድርጎ ማስተዋወቅ ነው። በአለፉት 15 ዓመቶች ኢትዮጵ ውስጥ በበቀሉት ጥቂት አረመኔዎች ምክንያት፣ የኢትዮጵያ አብዮት ስም ሊጎድፍ አይገባውም። ኢትዮጵያውያንም በጥቅል በአረመኔነት የሚታወቁበት ምክንያት የለም።

ለ. <u>የትጥቅ ትግል</u>

መኢሶን በአብዮቱ ዘመን የገበሬ ማህበሮች የፊውዳል ጦሮችንና ጥቃቶችን ለመቋቋም እንዲችሉና ወዝአደሮች፣ የቀበሌ ማህበሮች፣ ወጣቶች፣ ሴቶችና የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ሰራተኞች የኢሕአፓን የግድያ ዘመቻዎች ለመከላከል እንዲችሉ፣ ለትጥቅ መቀስቀሱና መታገሉ ትክክል ነው። በዚህም አኳያ የራሱ የተጋለጡ አባሎቹንና ወዳጆቹን ማስታጠቁ ተገቢ ነበር።

ይሁንና መኢሶን፣ የታጠቀ ሃይልን በተለይ በገጠር በተመረጠ ወይም በተመረጡ ሥፍራዎች የገነባ ድርጅት አልነበረም። ወይም የማፈግፈጊያና የመከላከያ አምባ ወይንም አምበዎች የሚበሉትን ከቶም የመሰረተ አልነ በረም። ድርጅቱ የመጨረሻ መጨረሻ ወደሕቡእ ሲገባ ሃይሉን ለመበታተን የተገደደውም፣ በመሰረቱ በዚሁ የመሰናዶ ጉድለት ምክንያት ነው።

ይህ ጉድለትና ስሕተት ከዚህ በላይ እንደተባለው ግን፣ የድርጅቱ አመራር ጭምር በእለት ተእለቱ ሕጋዊ ትግል ውስጥ በመጠመዱና ለትጥቅ ትግሉ ዝግጅት አስፈላጊውን ትኩረት ባለመስጠቱ ምክንያት ብቻ የተፈጸም አይደለም። መኢሶን ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ለትጥቅ ትግል የሰጠው ትኩረት እጅግ ዝቅተኛ ስፍራን የያዘ ስለነበር ነው።

መኢሶን በትጥቅ ትግል ረገድ ገና ሲጠሰነስ ጀምሮ የነበረው አቋም፣ ለተራዘመ የመሳሪያ ትግል የሚለው ነበር። በዚህም መሰረት መኢሶን በአነጻሩ፣ በቅድመ-አብዮቱ ዘመን በኢትዮጵያ ተራማጆች ውስጥ የተነሳውን „የፋኖአዊ“ (ፎኮይዝም) የትጥቅ ትግል መስመር ተቃወመ። ታገለ። እስከዚህም ድረስ አቋሙ ትክክል ነበር።

ፎኮይዝም፤ ስፋትና ጥልቀት ያለው የፖለቲካ ሥራ በቅድሚያ ባይሰራም፤ ጥቂት ሰዎች መሳሪያ ይዘው ጫካ በመግባትና የታጠቀ ፕሮፓጋንዳ በማድረግ፤ በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት ለመጣልና ሥርዓቱን መለወጥ ይቻላል ብሎ የሚያምን ነው። መኢሶን ይሕንን ስልት በአንድ በኩል ፖለቲካን ለጠብመንጃ ታዛዥ የሚያደርግ ሲሆን፤ በሌላው በኩል ሕዝቡን ተክቶ ሥርዓትን ለመለወጥ የሚደረግ ትግል በመሆኑ ምክንያት ተቃወመው።

ይሁንና፤ መኢሶን በበኩሉ ደግሞ፤ ለረዥሙ የመሳሪያ ትግል ያደረገው ይህ ነው የሚባል ዝግጅትና ድርጅት አልነበረም። አንዳንድ ጅምሮች የነበሩ ቢሆኑ፤ ከዳር ሳይደርሱ የቀሩ ናቸው።

መኢሶን ለምሳሌ ያህል በ1962 ዓ.ም. ፤ የመሳሪያ ትግል ለመጀመር የሚያስችለውን ሃይል ለማሰልጠን ከቻይና መንግስት ጋር የተነጋገረ ቢሆንም፤ ተግባራዊ ሳያደርገው ቀረ። ቀጥሎም በመስከረም 1963 ዓ.ም.፤ በምዕራብ ኢትዮጵያ የትጥቅ ትግል ለመጀመር የሚያስችሉ ቅድመ-ዝግጅቶችን ለማድረግ፤ አባላቱን ወደሱዳን ላከ። ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ጋር በመገናኘት አንዳንድ ሥራዎች በሱዳን አገር ውስጥ ተጀመሩ። ይሁንና የየካቲት አብዮት በፈነዳበት ጊዜ እነዚሁ ለዚሁ ሥራ የተመደቡ አባሎች በምዕራብ ኢትዮጵያ በሕጋዊ የሥራ መስክ እንዲሰማሩ በመደረጉ፤ ጉዳዩ በጅምር ተተወ።

በሁዋላም ከትግል ስልት ለውጥ ጋር በተያያዘ መኢሶን በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ ጭቁን ብሔሮች ጋር በመመተባበር የትጥቅ ትግል እንቅስቃሴ ቢጀምርም፤ ቅድመ-ዝግጅቱ የተሟላ ስላልነበር ፍሬ ሳይሰጥ ቀርቷል። ከዚያም በማከታተል በየተራ በሱማሌ ከሚገኙ የብሔረሰብ እንቅስቃሴዎች፤ ከህግሐኤ፤ ከህወሐትና ከኢሕዲን ጋር

ስለትጥቅ ትግል ትብብር ውይይቶች ተደረጉ። ይሁንና እነዚህንም፣ በተለያዩ ምክንያቶች ለመቋጠርና ከዳር ለማድረስ አልተቻለም።

እነዚህ የተዘረዘሩት ሙከራዎች ቢኖሩም፣ መኢሶን ባጠቃላይ ለትጥቅ ትግል የሰጠው ስፍራ ዝቅታኛ እንደሆነ የሚካድ አይደለም። ከዚህም የተነሳ መኢሶን በአንድ በኩል ባጠቃላይ ሲያነቃቸው፣ ሲያደራጃቸውና እስከተወሰነ ደረጃም ቢሆን እንዲታጠቁ ለታገለላቸው ሕዝባዊ ሃይሎች በውል የተደራጀ አመራርን ሊሰጣቸው አልቻለም። በሌላው በኩል እራሱን በቅጡ ለመከላከል የበቃ ድረጅት አልሆነም። ይህንንም፣ የመኢሶን መሠረታዊ ስህተት ነው ለማለት የሚቻል ነው።

ሐ. <u>የሥልጣን ጥያቄ</u>

ከዚህ በለይ የተነገሩት፣ መኢሶን „ንቃት፣ ድርጅት፣ ትጥቅ“ በማለት ያወጠውን የሕዝባዊ ሥልጣን አያያዝ መስመር በተግባር የተረጎመው፣ ይበልጡን ሕዝባዊ ድርጅቶችን በሕጋዊ መድረክ በማደራጀት እንደሆነ ያሳያሉ። በዚህም ጊዜ፣ ለቀጣዩ ትግል ያስፈልጉ የነበሩትን የሕቡእ አካሉን በማጠናከርና ለትጥቅ ትግል በማዘጋጀት ረገድ የሰራው እጅግ ዝቅተኛና ከቶም የማይመጣጠን እንደነበር በተጨማሪ ተመልክቷል።

መኢሶን ይህንን ስህተት የፈጸመው ለጉዳዩ በቂ ትኩረት ስላልሰጠው ብቻ አይደለም። በዚህ አኳያ በተጨማሪ ሁለት ጉዳዮችን መመልከት አስፈላጊ ነው። እነዚህም በብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ውስጥ የሥልጣንን ጥያቄ በሚመለከት የሰፈረውንና የኢማሌድህ ጉዳይ ናቸው።

መኢሶን ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ፣ ሕዝባዊ ሥልጣን በተደራጀና በታጠቀ የሕዝብ አመጽ የሚመጣ መሆኑን አምኖና ተቀብሎ የተነሳ ድርጅት ነበር። ይሁንና መኢሶን ከደረጉ ጋር ጊዜያዊ ትብበርን በመሰረተበት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መሰረት፣ ፕሮግረሙ፡-

> „ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮታችን ገፍቶ ድልን ሊቀዳች የሚችለው በአገሪቱ የሚገኙ ጸረ-ፊውዳልና ጸረ-ኢመፔሪያሊሲት ሃይሎች በፓርቲዎቻቸውና በሌ ሎቹ ድርጅቶቻቸው አማካይነት...ትግላቸውን የሚያስ ተባብሩበት ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ሲኖር ብቻ።“

ነው በማለትና፤ ቀጥሎም

> „የዚህ አብዮታዊ ግንባር ድል ዋስትና የሚኖረው የወዝአደሩ ፓርቲ ተደራጅቶ፤ ተጠናክሮና ታግሎ የግንባሩን አመራር ሲጨብጥ“

ነው በማለት ተገለጸ።

እነዚህ ጽንሰ ሃሳቦች በመሰረቱ ትክክል ቢሆኑም፤ ፕሮግራሙን ያወጀው የወቅቱ የሥልጣን በለቤት ያው ደርግ የነበረውን ያህል ደግሞ፤ የሥልጣን ጥያቄ በፕሮግራሙ እንደተመለከተው በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሊፈታ እንደማይችል ግልጽ ነበር።

ይህም ሆኖ መኢሶን የሕዝብ ሰፊር ለሥልጣን ፍልሚያ እነዲበቃ በንቃትና በድርጅቱ መጠናከር እንዳለበት አመነ። ለዚህም ከትብብሩ የመጀመሪያ ቀኖች አንስቶ በተገኙት ሕጋዊ መድረኮች ጭምር ሁሉ ለመጠቀምና የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝቦች ንቃትና ድርጅት ለማጠናከር ተሰማራ። ሠራ። አብዮቱንም የተቻለውን ያህል አራመደ።

በሕጋዊ መንገድ የተሰሩት ሰፊ ሥራዎች ሕዝብ ለሥልጠን ፊልሚያ በሚያደርገው ዝግጅት አኳያ አስፈላጊ የነበሩትን ያሕል ግን፤ <u>በራሳቸው</u> ሰፊውን ሕዝብ ለሥልጣን ንጥቂያ የሚያበቁት አልነበሩም። የተገኘው የሰፊው ሕዝበ ንቃትና ድርጅት ለሕዝባዊ አመጽ ፍልሚያ እንዲበቃ በተጠናከረ የሕቡዕ ድረጅትና ተጥቅ መቋጠር ነበረበት። መኢሶን ይህንን ሳያደርግ ቀረ።

መኢሶን በትብብሩ ጊዜ ከዚህም በተጨማሪ፤ ከሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ተቋሞች አልፎ በሚንስትርነትና በሌሎች መንግሥ ታዊ ከፍተኛ አካሎች

ውስጥ መገኘቱ፤ የሕዝባዊ ሥልጣን አያያዝ መስመሩን በሥልጣን መጋራት ስልት የተካው አስመሰለው። ይህ መሆኑም፤ የድርጅቱ መስመር በራሱ፤ በ አባሎቹና በወዳጆቹ ዘንድ ሳይቀር፤ እንዲደበዝዝና ግልጽ እንዳይሆን አድረጓል።

በትበብሩ ዘመን ሌላም ደግሞ፤ መንግሥቱ ሃይለማርያምና ተባባ ሪዎቹ አብዮታዊ ሰደድ በተሰኘው ድርጅት ተደራጅተው ቀረቡ። „የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ሕብረት“ (ኢማሌድህ) የተባለውንም ድርጅት፤ ሰደድን ጨምሮ በወዝአደር ሊግ በማሌሪድ በኢጫትና በመኢሶን አባልነት፤ ከየካቲት 1969 ጀምሮ መመስረት ተጀመረ። ቀጥሎም ለውህደትና ለወዝአደሩ ፓረቲ ባስቸኳይ መመስረት መቀስቀስ ተያዘ። በዚሁም ለማለት ይቻላል፤ ባንድ በኩል ከደርግ ጋር ሂሳዊ ድገፍ፤ እዚያው በዚያው ከደረግ/ሰደድ ጋር ደግሞ „ሕብረት የሚባልበት ሁኔታ ሰፈነ።

የኢማሌድህ መስራች ድርጅቶች የጋራ መገለጫና መርሃ ግብር የካቲት 18 ቀን 1969 ወጣ። የመኢሶን ሰፊ ኮነፈረነስ እንደሚታወቀው፡ በመጋቢት 1969 ተደረገ። ኮነፈረንሱም በዚህ ረገድ የተፈጠረውን አደገኛ ሁኔታና ባጠቃላይ ያንዣበበውን የጸረ-አብዮት ሁኔታ ከገመገመ በሁዋላ ንቅናቄው የትግል ስልት ለውጥ እንዲያደርግ ወሰነ። አያይዞም፤ መኢሶን በውጭና በኢማሌድህ ውስጥ በተለይም በዴሞክራሲያዊ መብቶች፤ ራስን በራስ በመቻልና በብሔራዊ ነጻነት ጥያቄዎች ዙሪያ የሚያደርገውን ቅስቀሳ ይበልጥ እንዲፋፋም ወሰነ።

መኢሶን በውሳኔው መሰረት ምንም እንኳን በራሱ በድርጅቱና በኢማሌድህ ውስጥ ግልጽ አቋም ቢወስድም፤ ስለኢማሌድህ ወደውጭ በይፋ የሚያራምደው ቅስቀሳ የኢማልዴህ ድርጅቶች ተዋህደው የወዝአደሩን ፐርቲ

ለመመስረት እንደሚችሉ የሚያስተጋባ ነበር። ብሎም ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር እንደሚቻል የሚያሰመስል ነበር።

ይህ በዚህ እንዳለ፤ መኢሶን የመጋቢት ኮንፈርንሱ በተደረገ በአራት ወሩ - በነሃሴ 1969 የትግል ስልት ለውጥ አደረገ። በዚህም ጊዜ ውስጥ፤ በጥድፊያ እንዲዘጋጅ ተገድዶ ነበር።

በሕጋዊ ርብርቦሽ የሰለለው የህቡዕ አካል ሃይሉና የጥድፊያ ዝግጅቱ፤ በንቅናቄው ላይ የተሰነዘሩትን ጥቃቶች ለመቋቋም የሚያስችሉ አልነበሩም። ስለሆነም፤ መኢሶን በቀላሉ ተጠቃ።

## 4. ሌሎች ስህተቶች

### ሀ. የዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ

መኢሶን የዴሞክራሲያዊ መብቶችን ጥያቄ „ንቃት፤ ድርጅት፤ ትጥቅ" ከሚለው ጥያቄው በላነሰ እንዳነሳው ከጽሁፎቹ ይታያል። ይህ ጥያቄ የሕዝብ ድርጅት ፅ/ቤት በሚቋቋምበት ዘመን፤ „አብዮት መድረክ „ በተሰኘው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አምድ ላይ፤ በተለይም በመኢሶንና በኢሕአፓ መካከል ሰፊ ውይይት የተካሄደበት ጉዳይ ነው። እንደዚሁም፤ በሚያዝያ 13 ቀን 1969 በወጣው በብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ውስጥ፤ አስፈላጊነቱ እንደሚከተለው የተገለጸ ጉዳይ ነበር።

> „ሕዝብ በአብዮቱ መግፋት የሚችለው ነቅቶ፤ ተደራጅቶ፤ ታጥቆ ለትግሉ የተሟላ ዝግጅት ሲኖረው ብቻ በመሆኑና ይህ ዝግጅት የሰመረ ውጤት ሊሰጥ የሚችለው የሰፊው ሕዝብ ወገኖች በሙሉ ለመማር ለማስተማር፤ ለመደራጀት ለማደራጀት፤ አስፈላጊ የሆኑት ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለ አንዳች ገደብ ከሥራ ላይ ሲወሉ ብቻ ስለሆነ፤ ጸረ-ፊውዳል፤ ጸረ-ቢሮክራሲያዊ ቡርዧ፤ ጸረ-ኢምፔርያሊሲት ሃይሎች በሙሉ የመናገር፤ የመጻፍ፤ የመሰብሰብ፤ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፤ የመደራጀትና የመሳሰሉት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ባስቸኳይ ከሥራ ላይ ማዋል።"

ጽህፈት ቤቱን ያቋቋመው አዋጅ መግቢያም፤

> „ ... የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ስለወጣና ዲሞክራሲያዊ መብቶችም በኢትዮጵያ

ሕብረተሰብ ውስጥ ላሉ ጸረ-ፊውዳል፣
ጸረ-ኢምፔርያሊስትና ፣ ጸረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊ
ስት ለሆኑ ሃይሎች ሁሉ የሚለቀቁ ስለሆነ።

እያለ፣ ለጽ/ቤት መቋቋም የሰጠው አንደኛው ምክንያት፣

„የሰፊውን ሕዝብ መንቃትና መደራጀት የሚ
ያግዝና የዴሞክራሲያዊ መብቶችን በትክክል
በሥራ ላይ መዋል የሚቆጣጠር አንድ የሕዝብ
ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ማቋቋም አስፈ
ላጊ ስለሆነ"

የሚለውን ነበር።

ወደውጭ እስከዚህ ባይታወቅም፣ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምና የጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ በረቀቁበት በታሕሳስ 1968 የዲክራሲያዊ መብቶች አዋጅም አብሮ ተረቀቀ። የተረቀቀው አዋጅ - በ አብዮቱ መንፈስ ለጸረ-ፊውዳል ጸረ-ኢምፔሪያሊስት ሃይሎች ጋዜጦችን እስከማውጣትና ፓርቲዎችን እስከማቋቋም የሚደርሱ መብቶችን የሚያረጋግጥ ነበር። በወቅቱም፣ የጽ/ቤቱ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እስኪቋቋም ድረስ፣ በዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ ላይ „ በአብዮት መድረክ" እና በውይይት ክበቦች መድረክ ላይ ይፋ ውይይት እየተደረገ እንዲቆይ ከስምምነት ላይ ተደረሰ። ውይይቱ በዚሁ መንፈስ ተከፈተ።

የዲሞክራሲ መብቶች አዋጅ ያልታወጀበት ምክንያት ብዙ ናቸው። ዋናው ምክንያት የራሱ የደርጉ ባህሪይና ተፈጥሮ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ተራአማጆች በዚህ ጥያቄ አኳያ አንድ ግንባር ሆነው የተባበረ ግፊት ለማድረግ አለመቻላቸው፣ አንሰተኛ የማይባል አሉታዊ አስተዋጽኦ እንደነበረው የማይካድ ነው።

ይሁንና፣ ወደመኢሶን ስንመለስ ደግሞ፣ መኢሶን ባጠቃላይ ለዲሞክራሲያዊ መብቶች መለቀቅ ከፍተኛ ቅስቀሳ ያካሄደ ቢሆንም፣ ተረቅቆ የሚገኘውን የዲሞክራሲ መብቶች አዋጅ በይፋ ለሕዝብ አስተዋውቆ በስራ ላይ እንዲውል በመጥራት እንዳልቀሰቀሰና እንዳልታገለ እንመዘግባለን።

ረቂቁ በመጀመሪያ፣ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች፣ ከበሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ጋራ አብሮ ሳይወጣና ሳይታወጅ ቀረ። ቀጥሎ በተራማጁ ሰፈር ውስጥ በተፈጠረው መከፋፈልና ልዩነት ላይ እየተሳበበ እንዲቆይ ተደረገ። ከዚያም፣ በመንግሥቱ ባንድ በኩልና በዓለ ማየሁ ሃይሌ/ሞገስ ወልደሚካኤል መካከል የነበሩት ትንቅንቆች እንደምክንያት ተሰጡ።

የመንግሥቱ ሃይለማርያም/አለማየሁ ሃይሌ-ሞገስ ወልደሚካኤል ትን ቅንቅ ጥር 26 ቀን 1969 በመንግሥቱ አሸናፊነት አበቃ። መንግሥቱ ጥር 27 ዕለት በአደባባይ ወጥቶ፣

> „ … ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በይፋ እናረጋግጣለን።
> … ሰፊው ሕዝብ በብዮቱ ለሚያስፈልገው ሙሉ ተሳ
> ትፎ ´ትጥቅና ዴሞክራሲ ለሰፊው ሕዝብ ወገኖች´ የሚ
> ለው መፈክር በሥራ ላይ ይውላል። … መፈክሮቹ የናንተ
> ብቻ ሳይሆኑ፣ የጊዜያዊው ወታደራዊ መንግሥትና መለዮ
> ለባሾች መፈክሮች ናቸው"

በማለት ተናገረ።

ይሁን እንጂ ከዚህም በሁዋላ፣ አወጁ እንዳይታወጅ ልዩ

ልዩ ሰበቦች ይሰጡ ጅመር። መኢሶንም ከንግዲህ፤ ረቂቁን ይፋ አውጥቶ የደርጉን (ሰደድ) ክህደት የለመታከት ማጋለጥና ለዲሞክራሲ መብቶች ጸንቶ መታገል ነበረበት። ረቂቁ ለሕዝብ ማታገያ ተጨባጭ መሳሪያ በሆነ ነበር። መኢሶን ይህንን ሳያደረግ ቀረ። ሌላው ቢቀር፤ የአዋጁ ረቂቅ ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ ታትሞ የወጣው እጅግ ከረፈደና ድርጅቱ የትግል ስልት ለውጥ ካደረገ ከሦስት ወሮች በሁዋላ „ትግላችን ዜና“ በሚባለው በአውሮፓ ተማሪዎች ማህበር (አኢተማ) መጽሄት፤ በጥቅምት 1970 ነበር።

ለ. <u>የሌሎች ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ሃይሎች ጉዳይ</u>

መኢሶን ሂሳዊ ድጋፍ የሚለውን ስልት ከቀየሰበት ከየካቲት 1967 ጀምሮ ሆነ፣ ከደርጉ ጋር ጊዜየዊ ትብብርን ባካሄደበት ጊዜ የ 15 ወሮች ዘመን፣ በመላ ሃይሉ ያተኮረው በአርሶ አደሩና በወዝ አደሩ ላይ እንጂ፣ ለሌሎቹ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ሃይሎች ለሚባሉት ክፍሎች (ዝቅተኛና መካከለኛ የመንግሥት ሠራተኞች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ በለሙያዎች፣ ነጋዴዎች፣ መለዮ ለበሾች ...) ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ነበር ለማለት አይቻልም። ወደነዚህ ክፍሎች የተመለሰው እጅግ አርፍዶ፣ ከመጋቢት 1969 በሁዋላ ነበር።

በሌላው በኩል፣ በተለይ ስለንዑስ ከበርቴው መደብ ይደረጉ የነበሩት ግራ-ቀደም ገለጻዎችና ቅስቀሳዎች፣ በመኢሶንና በዚህ መደብ መካከል ሲኖሩ የሚገባቸውን ግንኙነቶች አፋልሰዋል።

የኢትዮጵያን ብሔራዊ ከበርቴ መደብ በሚመለከተው በኩል የፈጸመውን ስህተት፣ በአንድ በኩል የትኩረት እጥረት፣ በሌላው በኩል የግራ ቀደም ስህተት ልንለው እንችላለን። ስህተቶችም ያለጥርጥር፣ ከዚህ ማህበራዊ ክፍል መካከል በዙዎቹን ወደአብዮቱ ተቃዋሚነት የገፈተሩዋቸውና የጸረ-አብዮቱን ፊና እንዲቀላቀሉ ጭምር ያገዙ ነበሩ።

ስህተቶቹ እርግጥ በመኢሶን ብቻ የተፈጸሙ አይደሉም። አልነበሩም። በአንድ መልካቸው፣ ካጠቃላዩ የአብዮት ሂደት ጋር ተገናዝበው መታየት ያለባቸው ጉዳዮች ሲሆኑ፣ በሌላው ወገን ከመኢሶን ቁጥጥር ውጭ ሲፈጸሙ የነበሩ፣ ጉዳዮች

እንደሆኑም አብሮ መታየት አለበት። አንዳንዶቹን ብናስታውስ፤

ከብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አበዮት ፕሮግራም መውጣት በፊት በደርጉ ይወሰዱ የነበሩት ብዙ የውርስ እርምጃዎች በርካታ - ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ክልል ውስጥ ሊታቀፉ ይችሉ የነበሩትን ክፍሎችን አሸሽተዋቸው ነበር። ከነዚህ መካከል በተለይ ከታሕሳሥ 23 1967 ጀምሮ የታወጁት ሥርነቀል የሆኑ የውርስ አዋጆች (ታሕሳስ 23 ቀን 1967 - የባንኮች፤ የፊናንስ ድርጅቶችና የመድህን ኩባንያዎች፤ ጥር 26 ቀን 1967 - የምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ መደብሮች፤ ሐምሌ 19 ቀን 1967 - የትርፍ ቤቶች ውርስ፤ መስከረም 19 ቀን 1968 - የግል ት/ቤቶች ውርስ) ይገኙበታል። በሌላው በኩል፤ ለምሳሌ ያህል ከበሰተጀርባው በኢሕአፓ አመራር ይመራ የነበረው ኢማአማ፤ በግንቦት 28 ቀን 1967 ባደረገው ስብሰባ፤

> „ ... አውቶቡሶች፤ ከባድ የጭነት መኪናዎች፤ የቡናና የአደንጓሬ ለኪ ኩባንያዎች፤ ማተሚያ ቤቶች፤ የመስታ ወት ሥራዎች፤ የጫማ ፋብሪካዎች፤ የምግብ ማደራጃ፤ የጭነት መርከብና የአሳ ማጥመጃ፤ ትላልቅ ሆቴሎች እንደዚሁም በዝባዥ ሚሊዮናውያን ስር ያሉ ሆስፒታሎ ችና የግል ት/ቤቶች ተወርሰው በሰፊው ሕዝብ ቁጥጥር ስር መዋል አላባቸው ...“

የሚለውን ውሳኔ እስከማሳለፍ ድረስ ሄዶ እንደነበር የሚታወስ ነው።

በተጨማሪም፤ በተለይ የመሬት አዋጅ ከታወጀ በሁዋላ አንዳንድ ዘማቾች፤ አንዳንድ የደረግ አባሎች፤ የሰራተኛ ማሕበሮች፤ የገሬና የቀበሌ ማሕበሮችና ...

ወዘተ. በየስፍራው ይወስዱ.ቸው የነበሩ ወፍጮ ቤቶች፣ የእርሻ መሳሪያዎች፣ የሆቴሎችና የቡና ቤቶች፣ የተሽከርካሪዎች፣ የፈረስ ጋሪና ጸጉር ማስተካከያ ሱቆች ውርስ ታሪኮች ሀሉ ይታወሳሉ።

መኢሶንን በሚመለከተው በተለይም በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መሰረት ከደርጉ ጋር ጊዜያዊ ትብብርን ከመሰረተ በሁዋላ፣ እነዚህ የዴሞክራሲያዊ አብዮት ሃይሎች እንዲረጋጉና በለውጡ እንዲተማመኑ ለማድረግ የወሰደው እርምጃ እንደሌለ እንገነዘበለን። ይህም እራሱን - የአብዮቱን በሔረዊ ዲሞክራሲያዊ ባህርይ የሚጻረር እጥረት ነበር።

> „የኢትዮጵያ ነጋዴዎች፣ ባለኢንዱስትሪዎችና እንዲሁም በሌሎች ለሀገር የሚጠቅሙ የግል ሥራ መስኮች የተሰማሩ ዜጎች፣ መንግስት በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ለአገሪቱ እድግት ተገቢ ድርሻቸውን እያበረከቱ ራሳቸውንም እንዲቅሙ አስፈላጊው እርዳታና ማበረታቻ መስጠት“

ማለት ለሰፈረው ትኩረት ሰጥቶ እንዳልታገለ የሚያሳይ ነው።

በሌላ በኩል ትርፍ ቤቶችን የወረሰውን የሃምሌ 19 ቀን 1967 አዋጅ በማርቀቅ ሆነ እንዲወጣ በመገፋፋት መኢሶን ያልተሳተፈ ከመሆኑ በላይ፣ አወጁ ከወጣም በሁዋላ አቢይ ጉድለቶች እንደነበሩበት መኢሶን ይቀበል ነበር። በተለይም የመኢሶን አበሎች ባስፈጻሚነት በተሰማሩበት ጊዜ በተገኘው የስራ ልምድ ተመስርቶ፣ መኢሶን በስራና ቤቶች ሚኒስቴር በኩል የትርፍ ቤቶች ውርስ አዋጅ እንዲሻሻል ሃሳብ አቅርቦ ነበር።

ይሁንና፤ መኢሶን ይህንኑ ለሕዝብ አላሳወቀም። በተጨማሪም እንኳን የራሱን ሃሳብና አማራጭ ዘርዝሮ በይፋ ለማቅረበ ቀርቶ፤ የአዋጁን ጉድለቶች እየተነተነ አልገለጸም። አልተቸም።

መኢሶን እንደዚሁም፤ ሌሎቹን (የሸቀጣ ሸቀጥ ድርጅቶች፤ የግል ት/ቤቶች የመሳሰሉትን) የውርስ አዋጆች ሙሉ በሙሉ የሚደግፍ አልነበረም። ሆኖም ተቃውሞውንና የራሱን አማረጭ ሃሳብ አሁንም ዘርዝሮ ያቀረበና በይፋ ያሰወቀ አልነበረም።

በተጨማሪም፤ የመኢሶን ስሕተት ይህም ብቻ አልነበረም። በዚሁ ጥያቄ አኳያ አንዳንድ አበሎቹና ወዳጆቹ በገለጻዎች ደረጃ ይሁን፤ ወይንም ባአደራጅነት በተሰማሩባቸው አካባቢዎች ያልተለጎሙ ጸረ-ብሄራዊ ከበረቴዎች ቅስቃሳዎችን አድርገዋል። በአንዳንድ ስፍራዎችም ሕዝባዊ ድርጅቶችን እያንቀሳቀሰሉ የውርስ እርምጃዎችን ወስደዋል። እንደዚሁም በንቅናቄው ልሳን <u>በሰፊው ሕዝብ ድምጽ</u> ላይ አንዳንድ ጊዜ የወጡት ጽሁፎች ከባድ ጸረ-ከበርቴ ቃና ነበራቸው። እነዚህም በእርግጥ ግራ-ቀደም ስህተቶች ነበሩ።

ሐ. <u>የውጭ ግንኙነት</u>

መኢሶን በቅድመ-አብዮትም ሆነ በአብዮቱ ዘመን የውጭ ግንኙነት ነበረው ለማለት ከቶም የሚቻል አይደለም። እንደዚሁም ደግሞ፣ በውጭ ቋንቋዎች እየተዘጋጁ የሚሰራጩ የራሱ ጽሁፎች፣ መጽሄቶችና መግለጫዎች ... ወዘተ አልነበሩትም።

በቅድመ አብዮት ዘመን የውጭ ግንኙነት ነበረው ከተባለ፣ በውጭ ይገኙ በነበሩት የተማሪ ማህበሮች ሽፋን፣ በዘመኑ ከሚገኙት ትናንሽ የማርክሲስት-ሌኒኒስት ቡድኖች ጋር ነበር። በኢተዮጵያ ውስጥ ይገኙ ከነበሩት ድርጅቶች ጋር (የኤርትራ ግነበሮች፣ የአፋርና የኦሮሞ ድርጅቶች ... ወዘተ) የነበሩትም ግንኙነቶች እንደዚሁ በተማሪ ማሕበርና በግለሰብ ደረጃ እንጂ፣ በድርጅት ስምና መስመር ያደረግነው ግንኙነት አልነበረም። መኢሶን በአብዮቱ ዘመን በህጋዊ መስኮች ተሰማርቶ በሚሰራበት ወቅት ከሶሻሊስት ፓርቲዎችና መንግሥቶች ጋር ሰፊ ግንኙነቶች ተከፍተው የነበሩ ቢሆንም፣ ግንኙነቶቹን ከሕጋዊ ግንኙነቶች ውጭ ለማስፋትና የመኢሶን ቀጥተኛ ድርጅታዊ ግንኙነት ለማድረግ አልተሰራም።

የመኢሶን የውጭ ግንኙነት እንደዚህ ደካማ የሆነበት ዋና ምክንያት፣ አንድም የድርጅቱ የውጭ ግንኙነት አስተሳሰብ „አስቀድሞ እራስን በራስ መቻልና እራስን በራስ ሃይል አጠናክሮ መገኘት “በሚለው መርህ ላይ የቆመ ስለነበር ነው። ሌላም፣ በተለይ ሶቭየት ሕብረትንና ተከታዮቿን በሚመለከተው፣ ጸረ-ሶሻል ኢምፔርያሊዝም የሚለው የውስጥ አቋም ስለነበረው ነው ማለት ይቻላል።

ስለነበረም ሶቪየቶች ለምሳሌ ያህል በቅድመ-አብዮት ዘመን ለመቀራረብ ያደረጉትን ተዘዋዋሪ ግንኙነት ሳይቀበለው ቀረ። በሌላው በኩል ከሕዝባዊት ቻይና ጋር አንዳንድ ግንኙነት የተጀመሩ ቢሆንም፤ ተከታታይነት ኖሯቸው አልቀተጠሉም። እንደዚሁም ደግሞ፤ ለምሳሌ ያህል እንደ ኤርትራ ግንባሮችና ኢሕአፓን የመሳሉት በመካከለኛው ምስራቅና በአፍሪካ ቀንድ ከሚገኙ መንግስቶችና ከፍልስጥኤም ነጻ አውጭ ድርጅቶች ጋር በመቀራረብ ይህ ነው የማይባልን የፖለቲካ፤ የሞራልና የፖለቲካ ድጋፍ ያገኙ እንደነበር መኢሶን ቢያውቅም፤ አሁንም ከላይ በተመለከተው መርሆው ምክንያት እነዚህን ሁኔታዎች በጥርጣሬ ዓይን ይመለከት ስለነበር፤ በራሱ በድረጅቱ ስም አንዳችም ቀጥተኛ ግንኙነት ሳይገነባ ቀረቷል። ይህም፤ ሌሎች ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች በውጭ ግንኙነታቸው መኢሶንን በየደረሱበት እንዳሻቸው እንዲያስተዋውቁ እረድቷቸዋል።

የመኢሶን አቋም አንዳንድ ጊዜ ሲታይ፤ ንቅናቄው ሊያገኝ የሚችለውን የፖለቲካ፤ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ ቢነፍገውም፤ መኢሶንን ከአብዮቱ በፊትም ሆነ በሁዋላ፤ የማንም መሳሪያ እንዳይሆን አስችሎታል።

መኢሶን ጸረ-ሶሻል ኢምፔሪየሊዝም ትግል ይል የነበረውን፤ አቋም በተጨማሪ መርምሯል። የውስጡ ውይይት በተለይ የተነሳው፤ መኢሶን በጥቅምት 1980 ከህወሐት ጋር ባወጣው የጋራ መግለጫ፤

> በሥልጣን ላይ ያለው ጸረ-ሕዝብ መንግሥትና ይህንን
> ጸረ-ሕዝብ አቅፎና ደግፎ የያዘው የሶቭየት ኢምፔሪያ
> ዝም፤ የኢትዮጵያ ህዝብ የወቅቱ ዋና ጠላቶች መሆና
> ቸውን ሁለቱ ድርጅቶች ያምናሉ።

የሚለውን አቋም በማስተጋባቱ ምክንያት ነው።

የንቅናቄው አባሎች ሶሻል ኢምፔርያሊዝም የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ እንዲጠና ጠየቁ። በጥያቄው ላይ የውስጥ ውይይት ተደረገበት።

በተደረገው ውይይት ሶሻል-ኢምፔርያሊዝም የሚለው ስነሰ-ሃሳብ በርካታ የቲዎሪ ጉድለቶችን ያዘለና በአብዛኛው የሶቭየት መነግሥት የውጭ ፖሊሲ ዶክትሪንና አፈጻጸም ላይ ያተኮረ አመለካከት መሆኑን፣ ንቅናቄው ተገነዘበ። እንደዚሁም በዚህ ረገድ የቀረቡትን ሌሎች ትችቶችና ጥናቶች ለማመዛዘን በተደረገው ጥናት፣ ጽንሰ-ሃሰቡ በቂ የቲዎሪ ድጋፍ፣ አጥጋቢ ርዕዩተ አለማዊ መነሻና ተጨባጭ መረጃ ሳይኖረው የቀረበ መሆኑን አመነ።

ስለሆነም፣ በአንድ በኩል ሶቭየት ሕብረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና ጠላት ከሆነው ወታደራዊ መንግሥት ጎን በመሰለፍ የምትፈጽመውን ጣልቃ ገብነት እየታገለ፣ በሌላ በኩል ድርጅቱ ሲመሰረት ጀምሮ የነበረውንና አልፎ አልፎ በይፋ ያንጸባርቅ የነበረውን ጸረ-ሶሻል ኢምፔሪያሊዝም በሃምሌ 1981 ባደረገው የድርጅቱ ጉባዔ እንዲነሳ ወስኗል።

## 5. <u>ከሌሎች ስለሚቀርቡ ሂሶች</u>

### ሀ. <u>ቀይ ሽብር</u>

ቀይ ሽብር በመባል በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጸመውን አስቃቂ የግድያ ዘመቻ በአንድ መልኩ የጠቅላላው የኢትዮጵያ አብዮት ሂደትና ተፈጥሮ በማድረግ፤ በሌላውም መልኩ በመኢሶን ላይ በመለጠፍ ያልተጻፈና ያልተነገረ የለም።

„ዕውነት ጊዜ አለው“ እንደሚባለው፤ ዕውነት ገሃድ እስኪሆን ድረስ ጊዜን ጠየቀ እንጂ፤ ከኢትዮጵያ ድርጅቶች መሃከል ግድያን የትግል ዘይቤው ቋሚ ስልት አድርጎ ለረዥም ጊዜ የተጠቀመበት ኢ.ሕ.አ.ፓ እንደሆነ የታወቀ ሆኗል። በተጨማሪም መኢሶን በሂሳዊ ድጋፍ መስመር ከደረጉ ጋር ጊዜያዊ ትብብርን መስርቶ በሰራበት እስከ ነሓሴ 1969 ድረስ፤ በ 1970 ዓ.ም. በቀይ ሽብር ስም የተፈጸመውን ዓይነት አጠቃላይ የግድያ ዘመቻ እንዳልተካሄደ ነጻ ታዛቢዎች እየመሰከሩ ነው። ወደፊትም ገና ብዙ ሃቅ እንደሚወጣ በእርግጠኝነት ለመናገር ይቻላል።

መኢሶን ከደርጉ ጋር ተባብሮ በሰራበት ወቅት በገጠርና በከተሞች፤ በሕዝባዊ ድረጅቶች አማካይነት የትጥቅ ማስፈታት እርምጃዎች ተወስደዋል። በተለይም በኣዲስ አበባ የኢ.ሕ.አ.ፓ ነፍስ ግድያ እየተፋፋመ በመጣበት ወቅት ይህንን ለመቋቋም ከጦር ሃይሎለች፤ ከፖሊስ ሰራዊት፤ ከሕዝባዊ ድርጅቶችና ከሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት በተውጣጣ ሃይል የትጥቅ ማስፈታትና ነፍሰ ገዳዮችን በቁጥጥር ስረ ለማዋል አሰሳ መደረጉ ሃቅ ነው። በዚህም ወቅት ከመጋቢት 14 ቀን እስከ መጋቢት 18 ቀን 1969 በአዲስ አበባ በተካሄደው አሳሳ፤ ግርማ ከበደ የተባለ

የቀበሌ መሪ ስለፈጸመው አሰቃቂ ግድያና በሚያዝያ 22 ቀን 1969 ዓ.ም. የደርጉ የዘመቻ መምሪያና አንዳንድ ቀበሌዎች በወጣቶች ላይ ለፈጸሙት ግድያ ከላይ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ዘርዝረን ገልጸናል።

በ1970 በ„ቀይ ሽብር“ ስም የተካሄደውን ሰፊ የፍጅት ዘመቻ የመሩት፣ የአብዮታዊ ሰደድ መሪዎች እነመንግሥቱ ኃ/ማርያም፣ ለገሰ አስፋውና አባሪዎቻቸው  የወዝ አደር ሊግና የማሌሪድ ድረጅቶች ናቸው። በመሳሪያነት ያገለገሏቸውም በ አንድ በኩል ከኢሕአፓ እየፈለሱ ሰደድን፣ ወዝአደር ሊግንና ማሌሬድን የተቀላቀሉት ኢሕአፓዎች ነበሩ። በሌላ በኩልም „የኢሕአፓ አንጃ“ ይባል ከነበረው ቡድን ውስጥ የራሱን የኢሕአፓን ግድያ እየሸሸ የአረመኔው የሻለቃ ብርሃኑ ከበደ የቀኝ እጆች ሆነው ያገለገሉ የነበሩት ግለሰቦች ነበሩ። በመጨረሻም ከመኢሶን ከድተው „ቀይ ፋና“ የተባለውን ጋዜጣ አቋቁመው ከሰደድ ጋር የተባበሩት እነ ኤልያስ ኑርና እንዲሁም ዶ/ር ዓለም አበበን የመሳሰሉ ሰዎች ይገኙባቸዋል።

በ1970 የነዚህ ሃይሎች እርኩስ ህብረት የተመሰረተውና ወደ ፍጅት ግድያ የተሸጋገረው እያንዳንዳቸው በወቅቱ በነበራቸው የየቀቅል ምክንያቶች ነበር።

አብዮታዊ ሰደድ፣ ተቃዋሚዎችን ሁሉ ጨፍጭፎ ከማጥፋት የተለየ ግብ አልነበረውም። የሰደድ መንግሥት በዚሕ ወቅት በሱማሌ ወረራ፣ የኤርትራ ግንባሮች ብዙ ከተሞችን በመያዝ ባገኙት ድል፣ መ ኢሶን ጊዜአዊ አቋርጦ ወደተቃውሞ በመሻገሩና የኢሕአፓ የተቃውሞና የግድያ ድርጊቶች በከተሞች ውስጥ በመስፋፋታቸው ምክንያት፣ ሥልጣኑን እነደጨበጠ ለመቆየት የሞት ሽረት ትግል በማካሄድ ላይ ነበር። የወዝ አደር ሊግ

መሪዎች እነሸዋኝ ዳኝ በለጠ፣ ሽመልስ ማዘንጊያ፣ ሻለቃ ሽታዬ፣ ሻለቃ ድንቁና ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ … ቀደም ሲል ከኢሕአፓ ከድተው አብዮቱን የተቀላቀሉ የማሌሪድ መሪዎች እነተስፋዬ መኮመንንና ሃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ፣ ከመኢሶን የከዱት አነዶ/ር አለሙ አበበና ኤልያስ ኑር በሰደድ መንግሥት ውስጥ በሥልጣን ተሳታፊ ለመሆን ያሰፈሰፉ ነበሩ።

ከኢሕአፓ ተከታዮች መካከል የተወሰኑት ክፍሎች ከድርጅቱ እየፈለሱ የዚህ ርኩስ ህብረት መሳሪያዎች የሆኑ፣ አንድም በውስጣቸው በነበረው የርስ በርስ ግጭት፣ ምክንያት ነበር። ሌላም፣ ባጠቃላይ በተከፈተው የመንግሥት የግድያ ዘመቻ ምክንያት፣ ጥቂት የማይበሉት የኢሕአፓ አባሎች ሰደድን፣ የወዝ አደር ሊግንና ማሌሪድን በመጠጋት ከፍጅቱ ለመጠለልና ለመትረፍ ነበር።

የኢሕአፓን የውስጥ ግጭትና የርስ በርስ ግድያ በሚመለከተው፣ የኢሕአፓ አመራር እንደሚታወቀው ገና በ1969 ጀምሮ „ የኢሕአፓ አንጃዎች“ በሚላቸው በነጌታቸው ማሩ/ብርሃነ መስቀል ረዳ ወገኖች ላይ ሰፊ የግድያ ዘመቻ ከፍቶ፣ የ„አንጃውን“ አባሎች በመጨረስ ላይ ነበር። የዚሕኛው የኢሕአፓ አመራር ግድያ የመጀመሪያ ምሳር ማረፊያ ከሆኑት መሃል አንዱም ራሱ ጌታቸው ማሩ ነው።

በ1970 ዓመተ ምህረትን የፍጅት ዘመቻና ግድያ (ቀይ ሽብር) ያካሄደው የነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሃይሎች ጥርቅም፣ ከሞላ ጎደል እንደሚከተለው ተደራጅቶ ነበር።

ዋነኞቹ መሪዎቹና አቀናባሪዎቹ፣ ራሱ መንግሥቱ ሃይለ ማርያምና፣ የሰደዱ ለገሰ አስፋውና የወዝ አደር ሊግ

መሪ አባል የነበረው ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ ነበሩ። ለገሰ አስፋው የጠቅላላው ፍጅት መሪ ብቻ አልነበረም። በቀጥታ በስሩ በነበሩት ተረወርዋሪ ገዳይ ቡድኖች አማካይነት፤ ያሻውን ግድያ የሚፈጽም ነበር። በለገሰ ተወርዋሪ ገዳይ ቡድኖች ከተገደሉትም ታጋዮች መካከል ለምሰሌ ያህል ራሱ የደርግ አባል የነበረውን ሳምበል ገበያው ተመስገንን፡ የመኢሶን አባሎች የነበሩትን ግዛው ጅማንና ዶ/ር መኮንን ጆቴን ለመጥራት ይቻላል።

ሳለቃ ብርሃኑ ከበደን በሚመለከተው፤ ይህ ሰው በይፋ ባልታወቁ፤ „የቀይ ሽብር ዘመቻ ጠቅላይ መምሪያ“ ሊባል በሚችለው መስሪያ ቤቱ አማካይነት የፍጅቱ ዘመቻ አንደኛ መሪ ነበር ማለት ይቻላል። በቀበሌዎች ውስጥ ይካሄድ የነበረው የግድያ ዘመቻ ይመራና ይቀነባበር የነበረውም በደርግ ጽ/ቤት ውስጠ በነበረው በዚህ በብርሃኑ ከበደ ቢሮ አማካይነት ነበር። የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት የግድያና የስቃይ ጣቢያዊች እየሆኑ የመጡትም፤ ቀበሌዎቹ የብርሀኑ ከበደ የዘመቻ ቢሮ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እየሆኑ በሄዱበት በዚህ ሰዓት ነው።

በዚህም ጊዜ ውስጥ ሰደድ፤ ወዝአደር ሊግ፤ መሌሪድና „ቀይ ፋና“ የተሰኘው ቡድን በቀበሌና በአብዮት ጥበቃ ኮሚቴ ሊቀ መንበርነት፤ በከፍተኛ የቀበሌ ማሕበሮች ሊቀ መንበርነትና ካድሬነት የማሕበሮቹን አመራር ያዙ። በተያያዘም፤ የቀበሌዎችን ባህርይና አሰራር ጨርሰው በመለወጥ፤ የማህበሮችን ጽ/ቤቶች የእስር ቤት፤ የምርመራና የግድያ ሰፈሮች አድርገው አደራጁቸው። በዚህም አኳያ ቀንደኞች ከነበሩት መካከል ለምሳሌ ያህል፤ የከፍተኛ አንድ ሊቀ መንበር እርገጤ መድበውንና የከፍተኛ 15 ባሳዝነውን የመሳሰሉ የሰደድ አባሎች፤ መጥራት ይቻላል። ከወዝ አደር ሊግ አባሎችም መካከል የፖሊስ ወታደር ተስፋዬ (ከፍተኛ

3 የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር)፣ እና የከፍተኛ 4 እንዳለ (ሊቀ መንበር) እና ማንአየ (ካድሬ)፣ የከፍተኛ 9 ሊቀ መነበር ቀልቤሳን፣ የከፍተኛ 12 ሰለሞንን መጥቀስ ይቻላል። ሌላም የማሌሪድ አባል የነበረውን የከፍትኛ 2 ሊቀ መንበር ሃጂንና ካድሬውን ማስታወስ ያስፈልገል። በከፍተኛ 22ም የግፉ ተዋናይ የነበሩት ከሰተ („የቀይ ፋና ቡድን አባል) እና የአንበሳ አውቶቡስ አብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር የነበረችውም የሰደድ አባል ይገኙበታል። ሌሎቹ ከኢሕአፓ እየፈለሱ ሰደድን፣ ወዝ አደር ሊግንና መሌሪድን የተቀላቀሉት የኢሕአፓ ተከታዮችና „አንጃዎች" ናቸው። እነዚህኞቹ በተለይ በሻለቃ ብርሃኑ ከበደ ስር ሆነው በጠቋሚነት፣ በገራፊነትና በገዳይነት የተሰማሩ ነበሩ።

በ1970፣ በ"ቀይ ሽብር" ስም የተካሄደውን ግድያ የፈጸሙት እነዚህ ክፍሎች ስንት ታጋይ ወጣቶችን፣ ምሁሮችን፣ ሰራተኞችን፣ አገር ወዳድና ዴሞክራት ግለሰቦችንና የጭቁን ብሔረሰቦችን ታጋዮችን ጨፈጨፉ። በኢትዮጵያ ምድር ጠቅላላ ሽብርን አስፍነው፣ አገሪቱን ከል አለበሷት።

በ1970 ዓ.ም. ይህ አጠቃላይ የመንግሥት፣ የድርጀቶችና ከድርጅቶች የፈለሱ ግለሰቦች ሽብር የተካሄደው፣ መ ኢሶን በነሃሴ 14 ቀን 1969 የትግል ስልት ሰውጥ ካደረገ ከወራት በሁዋላ ነው። መኢሶን በዚህ ጊዜ፣ በተጠቀሱት ሃይሎች ጥርቅም ከፍተኛ ጥቃት ከወረደባቸውና ከተፈጸመባቸው ድረጅቶች አንዱ ነው።

ይህም ሆኖ ደግሞ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚታገሉት የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ግድያና የከተማ ሽብር ፈጠራ እንደፖለቲካ የትግል ስልት ያስተዋወቀና ለረጅም ጊዜም በሥራ ላይ በሰፊው ያዋለው የኢሕአፓ አመራር

እንደነበር የሚያጠያይቅ አይደለም።

ይህም የኢሕአፓ ሽበር ፈጠራ የትግል ስልት፣ተቃዋሚ ሃይሎች ላይ ብቻ ያነጣጠረም አልመነበረም። በራሱ በድርጁ ውስጥ አመራሩና በተለያዩ አቋሞች ተቃውመውና ውስጣዊ የድርጅት ዴሞክራሲየዊ ሕይወት አለመኖሩን ባወገዙት አባሎቹም ሳይቀር እንደመደምሰሻና እንደማፈኛ ስልት የተ ጠቀመበትም ጭምር ነበር። በዚህ አኳያ ዴሞክራሲያዊ ውይይት በመጠየቃቸውም ሆነ በጥርጣሬ ብቻ የኢሕአፓ አመራር የገደላቸውን የራሱን አባሎች - እነጌታቸው ማሩን፣ ይርጋ ተሰማን፣ ጸሎተ ሕዝቅያሰን መጥቀስ ይቻላል።

ይህንን ስንመለከት፣ የኢሕአፓ አመራር የውስጥ ቅራኔዎችና ልዩነ ቶች አፈታት ስልት፣ ከደርጉ ዘይቤ በምንም የማይለይ ነበር ለማለት የሚቻል ነው። እንደ እውነቱም ከሆነ፣ ከልዩነቶች በራቁ ምክንያቶች ጭምር የኢሕአፓ አመራር የራሱን ታጋዮች ሕይወት መቀንጠስ የጀመረው ገና የጦር ትግሉን ለመጀመር ወደአሲምባ በሚጓዝበት ወቅት፣ ከድርጅቱና ከጦር መስራች አባሎቹ መካከል አንዱ የነበረው ቢንያም አዳነ፣ በድርጅቱ መሪ በብርሃነ መስቀል እንዲረሸን በተደረገ ጊዜ ነበር።

ይህንን ለጊዜው እዚህ ላይ ብናሳርፈው፣ በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ፣ በተለይም በ1968 አጋማሽ ጀምሮ የኢሕአፓ ፖለቲካ መስመር እየተጋለጠ መጣ። በፖለቲካ ትግል ዕምነት ያጣውና ለሥልጣን እጅግ የተጣደፈው የኢሕአፓም አመራር በከተማ ወጣቶች አማካይነት በመጀመሪያ የጠረባ (የድብደባ) ከዚያም ተሸጋግሮ የግድያ ቡድኖችን ማቋቋም ጀመረ። በአመራሩ ውሳኔና ብያኔ፣ የግድያ ዘመቻው በሰራተኞች፣ በቀበሌ ማህበራት፣ መሪዎች፣ በምሁሮች፣ በሴቶች፣ በወጣቶችና

በሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት ሰራተኞች በተለይም በመኢሶን ላይ ተከፈተ።

የኢሕአፓ አመራር ግድያንና የከተማ ሽብርን የጀመረው በአጋጣሚ አይደለም። ወይም የሁዋላ ሁዋላ እንደተባለው በተከላካይነትም አይደለም። አመራሩ „የከተማ ትጥቅ ትግል" አስፈላጊ ነው ብሎ በማመኑና በመወሰኑ ነበር። ለዚሁም፤ ገና በ1968 በዲሞክራሲያ „ልዩ በዓላዊ እትም" - ነሃሴ 26 ቀን 1968

> „ማናቸውም ሰሻል አብዮት የግድያ ሒደትም ነውና፤ (ኢሕአፖ) ለትጥቃዊ ትግል ሲያካሂድ የነበረውን ዝግ ጅት እጅግ በተፋጠነ መንገድ ያከናውናል። ጠላቶ ቹንም ይመታል።"

እያለ ያስተጋባውን „የግድያ ሂደት" አዋጅ ማጤኑ ብቻ ይበቃል።

ከዚህም በተጨማሪ በ1969 ዓ.ም. በዲሞክራሲያ ቅጽ 4 ቁጥር 11 (ቀን የሌለበት) የሚከተለውን አትቶ ነበር።

> „ኢሕአፓ ባሁኑ ሰዓት የሚያካሂደው በፍጹም ተራ ሽብር አይደለም። አብዮታዊ ሽብር ብቻም አይደ ለም። ... በከተማም በገጠርም የሚካሄደው የትጥቅ ትግል ነው። የገጠሩ የትጥቅ ትግል በአብዛኛው የሶስተኛው ዓለም አገሮች ዋነኛው የትግል መልክ ሲሆን፤ የከተማ የትጥቅ ጥግል በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመረኩዘን አስ ፈላጊነቱንና የሚቻል መሆኑን አምነን የጀመርነው ነው።"

የኢሕአፓ አመራር በዚህ እምነት የገባበትን የከተማ ግድያና ሽብር፤ መስከረም 16 ቀን 1969 ዓ.ም. የመኢሶንን

ወጣት ክንፍ (ኢአወን) አመራር አባል የነበረውን ገብረ እግዚአብሔር ተስፋዬንና የድርጅቱን አባሎች - አቡበከር አብዱልመጂድንና ክንፈ አስፋውን በገደለ ጊዜ ጀመረ። ከዚያም፤ መስከረም 21 እና ጥቅምት 2 ዕለት የመኢሶንን መሪ አባሎች የነበሩትን ዶ/ር ፍቅሬ መርድንና ገብረ እግዚአብሔር ሐጎስን ገደል።

መኢሶን በወሰደው የተከላካይነት እርምጃ፤ የማህበሮችና የከተማ ኗሪ ማሕበሮች መሪዎች የመከላከያ ቡድኖችን እንዲያቋቁሙና እንዲታጠቁ ጠየቀ። ለዚህም ታገለ። ኢሕአፓ አብዮቱ የወለዳቸውን ታጋዮች „አስፈላጊነቱና የሚቻል መሆኑንም አምነን የጀመርነው የትጥቅ ትግል ነው" እያለ በየአደባባዩ ሲቀነጥሳቸው፤ እነዚህ የሕዝብ ወገኖች አንዳችም መከላከያ ሳይኖራቸው እንደዝንብ እየረገፉ የሚያልቁበት ወቅት ነበር።

የኢሕአፓ የግድያ ዘመቻ ልጓም አጥቶ ቀጠለ። ብዙዎች ዛሬ ስማቸውን ዘርዝረን የማንጨርሰው ታጋይ ወጣቶች፤ የሰራተኛ፤ የከተማ ነዋሪዎችና የገበሬ ማህበራት መሪዎች፤ የመኢሶን አባሎችና ወዳጆች የሆኑ ምሁራን ባለሙያዎችና የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ሰራተኞች ... በግላጭ እየተቆሉ አለቁ። ስለሆነም፤ „አስታጥቁን አታስጨርሱን" የሚለው የአብዮቱ ወገኖች ጥሪ፤ የወቅቱ የአቤቱታ ጥሪ ሆነ። መኢሶን በአንጻሩ „ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት" ወደሚለው ቅስቀሳ፤ ጥያቄና ትግል ተሻገረ።

አስራ ሶስት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ማሕበራትና ሃያ የሰራተኛ ማሕበሮች የኢሕአፓ ግድያ ከጀመረ ከስድስት ወሮች በሁዋላ - የካቲት 27 ቀን 1969 ለመጀመሪያ ጊዜ ታጠቁ። የመከላከሉ እንቅስቃሴም መጋቢት 14 ቀን 1969

„የመንጥር ዘመቻ“ በተባለው የአሰሳና የትጥቅ ማስፈታት ዘመቻ ተጀመረ። በዚህ ወቅት መጋቢት 15 እና 16 እለት፤ ከኢሕአፓ መሪዎች ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ በተደረሰበት ጊዜ ራሱን ሲገድል፤ በሪሁን ማርዬና ማርቆስ ሐጎስ በተካሄደው የተኩስ ልውውጥ ሞቱ። እንዲሁም በርካታ የኢሕአፓ ነፍሰ ገዳዮች ሲያዙ፤ ሌሎችም እጃቸውን ሰጡ። ትጥቃቸውን ፈቱ።

የኢሕአፓ አመራር ከመጋቢት 18 በሁዋላም ቢሆን፤ በግድያ ፖሊሲው ቀጠለ። የኢሕአፓ ነፍሰ ገደዮች በተከተሉት ወሮች ውስጥ የቀጥፏቸው የመኢሶን አባሎች፤ ወዳጆች፤ የሰራተኞችና የሕዝባዊ ማህበራት መሪዎች፤ ባለሙያዎችና ወጣት ታጋዮች ጥቂት አልነበሩም። መኢሶንም በነሃሴ 14 ቀን 1969 የትግል ስልት ለውጥ እስካደረገበት ጊዜ ድረስ፤ የኢሐፓን የግድያ ዘመቻ በመከላከል ሲቋቋም ቆይቷል።

የሚያስገርም ከሆነ፤ „የሚያስገርመው“ እንበልና በ1969 ሆነ በ1970 የኢሕአፓ አመራር ጥይት አንድም „ፋሺስት ደርግን“ አልጣለም።

መኢሶን በነሐሴ 14 ቀን 1969 ከደርጉ ጋር መስርቶት የነበረውን ገዜያዊ ትብብር አቋረጠ። „ ቀይ ሽብር“ እጅግ አሰቃቂና አረመኔ በሆነ መልኩ በ1970 ቀጠለ። ምክንያቶቹንና አድራጊዎቹን ከዚህ በላይ በጭሩ የዘረዘርን ስለሆነ፤ እንድንመለስበት አያስፈልግም። እነዚያ ሃይሎች የፈጠሩት ርኩስ ህብረት የፈጸመው የፍጅት ግድያ ዘመቻ ከወረደባቸው ክፍሎች አንዱ መኢሶን እንደሆነም አመልክተናል።

ይህ በዚህ ቢሆን፤ መኢሶን የኢሕአፓን ግድያ ለመቋቋም ከመጋቢት 1969 እስከ ነሐሴ 1969 በወሰዳቸው

የመከላከል እርምጃዎች፤ ወይ በስሩ በነበሩ ሕዝባዊ ማህበራት ያለበለዚያም ባስታጠቃቸው ግለሰቦች አላፊዎች (ኢክሰስ) ተፈጽመው እንደነበር አይካድም። ሌላም የአብዮቱ ወገኖች ያለአንዳች መከላከያ ይጠቁ በነበሩበት ወቅት „ቀይ ሽብር ይፋፋም“ የሚለውን አራመዱል። ይሁን እንጂ፤ በ1970 ዓይነቱ የፍጅት ግድያ ዘመቻ በየመንገዱና በየአደባበዩ አልተካሄደም።

„የከተማ ትጥቅ ትግል“ በሚል በኢሕአፓ አመራር በተጀመረው ትግል ዘይቤ ምክንያት፤ አንድ ትውልድ ያፈራቸው ታጋዮች ከመኢሶንም ከኢሕአፓም በኩል ተሰው፤ አለቁ፤ ሌሎችም፤ በየእስር ቤቱ ተጉላሉ፤ ተሰቃዩ፤ ተሰደዱ። በዚህም ምክንያት፤ በሁለቱ ወገኖች መካከል አልደርቅ ያለ የታሪክ ጠባሳ ታተመ።ሽብሩ ከነረሱ አልፎ በዚህኛውም ሆነ በዚያኛው ድርጅት ውስጥ ባልነበሩ ግለሰቦች ተራማጆች፤ ዲሞክራቶች፤ አገር ወዳዶች፤ የጭቁን ብሄር ታጋዮች ድርጅቶች ላይ ሁሉ እንደወረደ የታሪክ ሃቅ ነው።

ከደረሰው ጥፋት ተገቢው ትምህርት መቀሰም ይኖርበታል። ሁለተኛም፤ የዛሬውና የመጭው ትውልድ የሃገር ፍቅር ስሜት ተድሶና በዲሞክራሲያዊ ውይይትና አስራር ዘዴዎች ታንጾ፤ ለሀገሩና ለወገኑ ለመታገል እንዲነሳሳ የማድረግ የታሪክ ሃላፊነት አለብን። የለፈው ታጋይ ትውልድ የሚካሰውም፤ የዛሬው ታጋዮች ካለፈው ትግል ትምህርትን ለመቅሰም ሲችሉና የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነት ለመሸከም ሲበቁ ነው።

## ለ. <u>የደርግ መጠናከር</u>

በመኢሶን ሂሳዊ ድጋፍ አቋም ላይ አንዳንዶች የሚያቀርቡት ሂስ „መኢሶን በዚህ መስመር ከደርግ ጋር በፈጠረው ጊዜያዊ ትብብር፤ ደርጉ ተጠናከረ“ የሚለው ነው። የሂሱም መነሻ ሃሳብ፤ `መኢሶን የገበሬ፤ የወዝ አደርና ቀበሌ ማህበራትን አጠናክሮ ካደራጀ በሁዋላ፤ ለደርጉ ጥሎለት ሄደ። ደርጉ ተጠቀመበባቸው’ የሚለው ነው።

እርግጥ ነው፤ መኢሶን ያነቃቸው ያደራጃቸውና እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ እንዲታጠቁ የታገለላቸው ድርጅቶች የሕዝብ የሥልጣን መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ ነበሩ። መኢሶን እነዚህን ሃይሎች እስከመጨረሻው ድረስ ሊመ ራቸውና ከደርጉ (ሰደድ) ጥቃት ፊት የማይበገሩ ሃይሎች አድርጎ ሊያቆማቸው አልቻለም።

ይሁን እንጂ፤ „ደርግ (ሰደድ) የተጠናከረው ድረጅቶችን በመጠቀም ነው“ የሚለው አስተሳሰብ ደግሞ፤ ከነገሮች ሂደትና ክንዋኔ ጋር የተገናዘበ አይደለም። መኢሶን ከደርጉ ጋር የመሰረተው ጊዜያዊ ትብበር፤ የቀድሞውን የገዥ መደቦች ለመጣልና የኢኮኖሚና የሶሻል መሰረታቸውን ለመገርሰስ ነው። ሌላው የትግሉ ገፅታ፤ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሥልጣን ደርጉን ሊተካ የሚችልበትን መሰረት ለማስፋትና ለማጠናከር ነበር። መኢሶን በዚሁ ስልት፤ ሕዝባዊ ሃይሎች እንዲነቁ ፤ እንዲደራጁና እንዲታጠቁ ታገለ።

ሕዝባዊ ድርጅቶች በአብዮቱ ዘመን ነፃ ህልውና የነበራቸውና፤ እንዲያውም በተጻራሪው ከቢሮክራሲውና

ከፖሊስ ሃይል ጋር ያካሂዱት የነበረው የፋመ ትግል፣ እነዚህን የደርጉን ሥልጣን መሰረቶች የሚተናነቁ ነበሩ። የደርጉ ቀጥተኛ ሥልጣን አስፈጻሚ ሃይሎች ቢረሎክራሲው፣ ፖሊሱ፣ ጸጥታውና ሠራዊቱ እንጂ፣ ሕዝባዊ ድርጅቶች አልነበሩም። በዚህ ሁኔታ የህዝባዊ ሃይል መሰረቶችን ማጠናከርና ከሕዝብ ጋር መሰለፍ፣ ደርግን ማጠናከር ማለት አልነበረም። በተቃራኒ ደርግንና አስፈጻሚ ክፍሎቹን መቋቋም ማለት ነበር።

ጥር/የካቲት 1969 ሰደድ የበላይነቱን በተቀዳጀ ጊዜ፣ የ አብዮትም የቅልበሳ ሂደት ተከፈተ። ነገር ግን ሕዝባዊ ድርጅቶች በዚያን ወቅት ሰደድ እንዳሻው የሚያዛቸውን የሚጠቀምባቸው አልነበሩም። እነዚያ አብዮቱ የወለደቸውና አብዮቱን የራሳቸው አድርገው ይመለከቱና ይሞቱለት የነበሩት ሕዝባዊ ድርጅቶች ሰደድ አብዮቱን እየከዳ፣ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝቦች ጥቅምና እየተጻረረና የራሱን ዘለቂ ስልጣን እያመቻቸ በመጣበት ወቅት፣ ለዲሞክራሲያዊ መብቶች፣ ለብሄረሰቦች መብቶች መታወቅና መከበር፣ ለራስን በራስ መቻልና ለብሄራዊ ነጻነት የማይናቅ ተጋሰድሎ አድርገዋል። መሪዎቻቸውና አባሎቻቸው ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለዋል።

ይህንን ታሪክ የሚረሳው አይደለም። በወቅቱ ለየትኞቹ አቋሞቸ እንደታገሉ ለማጤን፣ የመላ ኢትዮጵያ ሰራተኞች ማሕበር(መኢሰማ)፣ የአዲስ አበባ ቀበሌዎች አጠቃላይ ማሕበርና የሸዋ ክፍለ ሃገር ገበሬዎች ማሕበር ተወካዮች መኢሶን የትግል ስልት ካደረገ በሁዋላ፣ ከጥቅምት 14 እስከ ጥቅምት 17 ቀን 1970 በጋራ ባደረጉት ስብሰባ፣

„የውጭ ወራሪ ዛሬ የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ በጎሳና በሃይማኖት አለያይቶ ለማዋጋት በመጣር ላይ ሲሆን፡ ከውስጥ

> የሚገኙ አድሃሪዎች ደግሞ … የዴሞክራሲ መብቶ
> ችና የብሔረሰቦች እኩልነት እንዲታፈንና የብሔራዊ
> ዴሞክራሲ አብዮት ፕሮግራም በየደረጃው በሥራ
> እንዳይተረጎም ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ እየተሯ
> ሯዋጡ ናቸው።“

በማለት ያሳለፉትን ውሳኔ መስታወስና ማጤኑ ብቻ ይበቃል።

የደርግ የሥልጣን ባለቤት መሆንና ከአብዮቱ መቀልበስ ሂደት ጋር በተያያዘ፤ አብዮቱ የወለዳቸውና የሕዝባዊ ሥልጣን መሰረቶች ሊሆኑ ይችሉ የነበሩት ድርጅቶችና ሰደድ በተለያዩ ተጻራሪ ሰፈሮች ቆሙ። ሰደድ በተቀሩት የስልጣን ተቀናቃኝ ሃይሎች ላይ የግድያ ዘመቻውን እንዳካሄደው ሁሉ፤ በነሱም ላይ የጭቆና በትሩን አወረደባቸው። በቁጥጥሩ ስር ያዋላቸውና ማህበራቱን ተገኘር ለማድረግ የበቀው፤ እነዚያን በአብዮቱ የአበባ ዘመን ደርተው የነበሩትንና ከኢሕአፓ የግድያ ዘመቻ ተርፈው የነበሩትን ሕዝባዊ መሪዎች ከገደለ፤ ካሰረና ከረሸነ በሁዋላና የማሕበራቱን አመራር በሰደድ ሰዎች እጅ እየተካ ከተንሰራፋ በሁዋላ ነው።

የሰደድ ዋነኞቹ የስልጣን መሰረቶች እንደ እውነቱ ከሆነ፤ ከውስጥ የሲቭል/ወታደር ቢሮከራሲውና ከውጭ በሶቭየት ሕብረት መሪነት የደገፉት የውጭ ሃይሎች ናቸው። በዚህም አኳያ ዋናውን ሚና የተጫወተው ጉዳይ፤ ሰደድ በብቸኝነት ስልጣንን በጨበጠበት በጥር/የካቲት 1969፤ የሱማሌ ወረራ መነሳቱ ነበር። የሱማሌ ወረራ፤ ደርግን የወቅቱ „የናት አገር ወይም ሞት“ ጥሪ ባለቤትና መሪ አደረገው። ይህም <u>አንደኛ</u> የሰደድንና የአስፈጻሚውን ክፍል ወይንም የሲቭል/ወታደሩን ቢሮክራሲ መተሳሰር አፋጠነ።

የሱማሌ ወረራ ሁለተኛ፣ ለሰደድ መንግስት ከባድ የውጭ ወታደራዊና የጦር መሳሪያ ድጋፎች እንዲጎረፉለት ሁኔታዎችን አመቻቸ። ድጋፉ ከሶሸሰሊት አገሮች የመጣውን ያህል ደግሞ፣ ቢያንስ በሶቭየት ሕብረት ዙሪያ በሚሽከረከሩት መንግስቶች፣ ፓረቲዎችና ድርጅቶች ዘንድ ሶሻሊስታዊ ´ቡራኬ` አቀዳጀው። እንዲያም ሲል፣ ከዓለም አቀፍ ሃይሎች አሰላለፍ መድረክ አወጣው።

ሦስተኛ፣ „እናት አገር ወይም ሞት“ የሚለው ጥሪ የመደቦችንና የፖለቲካ ሃይሎችን አሰላለፍ ክልል አቆራርጦ ሕዝባዊ ክፍሎች ጭምር ከደርጉ ጀርባ እንዲሰለፉ አደረገ። የሰደድ መንግስት ይሔንንም ዙሮ ዙሮ የተጠቀመበት የዴሞክራሲን ጥያቄ የሚያነሱበትንና ሊያነሱበት የሚችሉትን ሃይሎች ለማፈራረስና ለመሰባበር ነው። በመጨረሻው ለይ ግን፣ የሰደድን መንግስት የመጨረሻ መጨረሻ አጠናክሮ ያቆመው የሶቭየት ሕብረትና የተከታዮቿ መንግስታት ከፍተኛ ድጋፍ መሆኑን አተኩሮ ማንሳት ያስፈልጋል። እነዚህ ሃይሎች እንደሚታወቀው፣ ለመንግሥቱ ሃይለማርያም መንግስት በጥቂት ወሮች ውስጥ በመቶ ሺሕ የሚቆጠርን ሰራዊት አሰለጠኑለት። የጸጥታ መስሪያ ቤቱንና ሃይሉን በአዲስ አደራጅተው አጠናከሩለት። ለመንግስቱ ሃይለማርያም ከነባሩ የአጼ ሃይለስላሴ መነግስት የተለዩና የራሱ „ፍጡር“ የሆኑ የሰራዊትና የጸጥታ ሃይል መሰረት ያስገኙለት ጉዳዮች በመጀመሪያ ረገድ እነዚህንና አነዚህን የመሳሰሉት የውጭ ድጋፎች ነበሩ። በነዚህ ጉዳዮች ውስጥ መኢሶን አንድም ተሳትፎ የለውም። በተቃራኒው፣ በታጠቅ ጦር ሰፈር ሚሊሺያው በሚቋቋምበት ጊዜ ለምሳሌ ያህል፣ መኢሶንን ለማግለል ሲባል የሕዝብ ድርጅት ጉደይ ጽ/ቤት ሰራተኞች ከጦር

ሰፈሩ በሰደድ ልዩ ትእዛዝ የታገዱ ነበሩ።

ደጋፊዎቹ የውጭ ሃይሎች የመነግስቱን የሰራዊትና የጸጥታ ሃይል ከመገንባታቸውም በተጨማሪ፤ በኢሰፓኮ፤ በኢሰፓና በመንግስቱ ሪፑብሊክ መመስረት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ እነደነበራቸው እንድናትት የሚያስፈልግ አይደለም። እነዚሕ ሃይሎች ከፓርቲ ግንባታ አንስቶ እስከ ሕገመንግስቱ መረቀቅ ድረስ በግልጽ እየተሳተፉ የመንግስቱንና የፓርቲውን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ በአግሩ ለማቆም ከፍተኛ ሚና እንደተጫወቱ የሚታወቅ ነው።

ሐ. <u>የሶቭየት ሕብረት መግባት</u>

አንዳንድ ሰዎች፣ አንዳንድ ጸሃፊዎችና አንዳንድ በኢትዮጵያ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች ለሶቭየት ሕብረትና ለተከታዮቿ መንግስታት በገፍ መግባት መኢሶንን ተጠያቂ እያደረጉ ይተቻሉ። ይህ ግን እንደብዙዎቹ በማኢሶን ላይ እንደሚነገሩት ታሪኮች ከእውነት የራቀ ነው።

በመጀመሪያና ከሁሉ በፊት፣ መንግስቱ ሃይለማርያም በጥር 26 ቀን 1969 የእነአለማየሁ ሃይሌ/ሞገስ ወልደሚካኤልን ቡድን አጥፍቶና ብቸኛው የደርግ መሪ ሆኖ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ፣ ሶቭየት ሕብረትና ተከታዮቿ ለኢትዮጵያ ይህ ነው የሚባል ድጋፍ እንዳልሰጡ የሚታወቅ ነው። የሶቪየቶቹ ፖሊሲ እስከዚሁ ጊዜ ድረስ „እያየህ ቆይ“ የሚለው ነበር። ወቅቱም እንደሚታወሰው፣ መኢሶን ከደርጉ ጋር ጊዜያዊ ትብብር መስርቶ ይሰራ የነበረበት ወቅት ነው።

ሶቭየት ህብረትና ተከታዮቿ መንግስቶች በዚህ ወቅት እንኳን የደርጉ አጋር ሆነው ሊሰለፉ ቀርቶ፣ የኢትዮጵያን አብዮትና መኢሶንን የሚያዩት በከፍተኛ ጥርጣሬ ነበር። ለዚህም ምክንያቶች ነበሩ። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አብዮታዊ ፕሮግራም እራሱ የተዘጋጀው በአብዛኛው በሕዝባዊት ቻይና ዲሞክራሲያዊ አብዮት ልምድ ላይ ተመስርቶ ነበር። ከዚህም በተያያዘ ጸረ-ፊውዳል ጸረ-ኢምፔሪያሊስትና ጸረ-ቢሮክራሲያዊ ከበርቴ የሚለው የአብዮቱ ባሕርይ አገላለጽ፣ „ወደ ሶሻሊዝም ለመጓዝ ካፒታሊስት ያልሆነ የእድገት ጎዳና“ ከሚለው የሶቭየት ህብረት ጽነሰ-ሃሰብ ጋር

እንደማይዛመድ፤ ለሶቭየት ህብረት የተሰወረ አይደለም። በመጨረሻም፤ በወቅቱ በኢትዮጵያ በአብዮቱ ሰፈር የሚገኝና የሶቭየት ህብረት ቡችላ የሆነ ድርጅት አልነበረም።

ይህ በዚህ ቢሆን፤ መኢሶን በተለይም በአብዮቱ ወቅት የውጭ ርዳታን በሚመለከተው ያራምደው የነበረው „ራስን መቻልና በራስ መተማመን“ አቋም፤ መኢሶን ጸረ-ሶቭየት ነው የሚለውን እምነት በሶቭየቶች ላይ አሳድሮ ነበር። እዚህም ላይ ሶቭየት ሕብረት በሁዋላ በመኢሶን መሪነታቸው የተወቁትን የመኢሶን መሪዎች በቅድመ አብዮት ዘመን ለመገናኘትና ለመወዳጀት ሞክራ ሳይሳካላት የቀረ መሆኑን ለማስታወስ ይቻላል። በወቅቱ ግንኙነት የነበረውና ወዳጅነትን መስርቶ የነበረው ይልቁኑ፤ የኢሕአፓ አመራር ነበር። የኢሕአፓ አመራር በ1968 ዓ.ም. ለተደረገው የሶቭየት ሕብረት ኮሚዩኒስት ፓረቲ ስብሰባ የድጋፍ መልዕክት አስተላልፎ እንደነበር የሚታወስ ነው።

የኢትዮጵያ አበዮት አገሪቱን ባጥለቀለቀበት በ1966 ዓ.ም. ሶቭየት ግንኙነቷን በማጠናከር ላይ የነበረችው ይልቁኑ ከሱማሌ መንግስት ጋር እንደነበር ይታወቀል። 1966 እንደሚታወሰው፤ ሶቭየት ህብረት ከሱማሌ መንግስት ጋር የ20 ዓመት የወዳጅነትና የትብበር ውል የተፈራረመችበት፤ የሱማሌን መንግስት በዘመናዊ የጦር መሳሪያ በከፍታኛ ደረጃ ማስታጠቅ የጀመረችበትና የሱማሌም መንግስት በምትኩ ሶቭየት ሕብረት በበርበራ ወደብ ላይ የባሕር ጦር ሰፈር እንደትገነባ የፈቀደበት ጊዜ ነው። ሰቭየት ሕብረት በተጨማሪ በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ሲል ጀምሮ በተዘዋዋሪ - በኩባ፤ በምስራቅ አውሮፓ አገሮች፤ በሶርያ፤ በኢራቅ፤ በደቡብ የመንና በፍልስጥኤም ነጻ አውጭ ድርጅት በኩል - ስትደግፍ የኖረችው፤ የኤረትራ ግንባሮችን ነበር።

የኢትዮጵያን አብዮት፣ መኢሶንና ሶቭየት ህብረትን በሚመለከተው በመጀመሪያዎቹ የአብዮት ሶስት ዓመቶች ውስጥ የነበረው ሃቅ ነው። ይህ ወቅት ሶቭየት ሕብረትም የኢትዮጵያን አብዮት ከመኢሶንና ብሎም ከሕዝባዊት ቻይና መስመር ጋር በማዛመድ፣ ለጣልቃ ገብነቷ ያልተመቻቸና ከቁጥጥሯ ነፃ በሆነ መንገድ የሚራመድ አብዮት ሆኖ ያገኘበት ወቅት ነበር።

መንግስቱ ሃይለማርያም በጥር 26 ቀን 1969 አሸናፊ ሆኖ ሲወጣ ግን፣ የስልጣኑ ባለቤት እንግዲህ አብዮታዊ ሰደድ የተባለው ድርጅት እንደሆነ ለሶቭየት ህብረት የተሰወረ አልነበረም። በዚሕ ሁኔታና በዚህ ሰዓት ከሰደድ ጋር ለመወዳጀት መጣደፏም፣ ከቶም እንደ እንግዳ ነገር ሊታይ የሚችል አይደለም።

ከጥር 26 የደርጉ ውስጥ ፍልሚያ በሁዋላ ሶቭየት ሕብረትና ተከታዮቿ መንግስቶች „እንኳን ደስ ያለህ" የሚለውን መልክታቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመንግስቱ ለማሽጎድጎድ ተሽቀዳደሙ። አምሳደሮቻቸው የቤተመንግስቱንና የውጭ ጉዳይ ሚነሰቴርን ደጃፎች አጨናነቋቸው። እንደዚሁም እስከ መጋቢት 1969 ድረስ ብቻ ሁለት የዩጎዝላቪያ፣ አንድ የቡልጋርያ፣ ሶስት የምስራቅ ጀርመን፣ አንድ የቼኮዝላቫኪያ፣ ሁለት የኩባ መልክተኞች ኢትዮጵያን (መንግስቱን) ባጭር ጊዜ ውስጥ ሲጎበኙ፣ የሶስት የምስራቅ አውሮፓ አገሮች የባህል ተጫዋቾችም መጡ፡ በመጨረሻም የኩባው መሪ ፊደል ካሰትሮ ራሱ መጋቢት 5 ቀን 1969 መጣ። መንግስቱ ሃይማርያም በበኩሉ፣ ከሚያዝያ 25 እስከ ግንቦት 2 ቀን 1969 ባለው ጊዜ ውስጥ፣ ወደሞስኮ፣ ሶርያና ሊቢያ ሄደ።

ነገር ግን ወቅቱ ከሱማሊያ ወረራ መነሳት ጋር የገጠመም ነበር። የፕሬዚዴንት ካርተር አስተዳደር በዚህ ሰዓት ከተወረረችው ኢተዮጵያ ጎን አለመቆሙና በተደጋጋሚ የተጠየቀውን የመሳሪያ ድጋፍና ሽያጭ አለመፈቀዱ፤ ሁኔታዎችን ለሶቭየት በገፍ መግባት በተጨማሪ አመቻቸ። ሶቭየቶች የመጨረሻ መጨረሻ እንደሚታወቀው፤ ከሶሎማሊያ ጋር የነበራቸው ግንኑነት እስኪበጠስ ድረስ ሄደው፤ ከመንግስቱ ሃይለማርያም ጋር ባላቸው ሃይል ተሰለፉ።

## በዚህ ሰዓት የመኢሶን አቋም ምንድርን ነበር?

መኢሶን ሶቭየት ሕብረትን በጥርጣሬ ዓይን ይመለከት እንደነበር ከዚህ በላይ አስታውሰናል። የመኢሶንም ፖሊሲ የተመሰረተው „በቅድሚያ ራስን በራስ መቻል“ በሚለው መርህ ላይ እንደሆነ ተብራረቷል። ሶቭየት ሕበረትና ተከታዮቿ ወደ ኢትዮጵያ መጉረፍ በጀመሩበትም ጊዜ፤ የመኢሶን አቋምና መስመር በወቅቱ በይፋ እነደተገለጸው የሚከተለው ነበር። (ይህም መጋቢት 15 ቀን 1969 „ ሶሻሊስት አገሮችና የኢትዮጵያ አብዮት“ በሚል ባወጣው የሰፊው ሕዝብ ድምጽ ቁጥር 53 እትም ውስጥ ይገኛል።)

> „በተራማጅ አገሮችና በኢትዮጵያ መካከል መቀራረብ እንዲኖር፤ ተራማጅ አገሮችና ድርጅቶች የኢትዮጵያን ብዮት ባሕርይ እንዲረዱና ለአብዮታችን ሃቀኛ ድጋፍ እንዲያበረከቱ መኢሶን በበኩሉ ሰፋ ያለ ቅሳሳ አካሂዷል። ይሕ ቅስቀሳ ዛሬ የኢትዮጵያ አብዮት በማግኘት ላይ ላለው ዓለም አቀፋዊ ድጋፍ መጠነኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ለማለት ይቻላል።
>
> በዓለም አቀፋዊነት መርሆ መሰረት የሚገኝ እርዳታ አስፈላጊ ይሁን እንጂ ለኢትዮጵያም ሆነ ለማንኛውም አገር ዋናው ነገር በራስ መተማመን ነው። እርዳታ ድጋፍ

> *እንጂ፤ መሰረት አይሆንም። ለእድገት ለሶሸሊዝም … ወዘተ ዋናው መሰረትና ዋስትና በራስ ሃይል መተማመንና ማንኛውንም ከዚህ አንጻር መመልከቱ ነው። ይህንን መረዳቱ በአንድ በኩል የአገሪቱን ክብርና ነጻነት ለጥቂት ጊዜያዊ ጥቅሞች ከመሸጥ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሶሻሊስትና የሌሎችንም አገሮች እረዳታ የኢትዮጵያ አብዮት ወሳኝ ጥያቄ አድርጎ ከመውሰድ ይጠበቀናል።*
>
> *የሶሻሊስት አገሮችና የሌሎችም የአለም ተራማጅ ሃይሎች ድጋፍ መገኘት ለኢትዮጵያ አብዮት በጣም አስፈላጊና ሲገኝም ደግሞ በጣም አስደሳች ነገር ነው። ይሁንምና በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ቢሆን፤ ምንም ያህል የኢኮኖማዊ፤ የፖለቲካዊና የማሕበራዊ ኑሮ ችግሮች ቢኖሩም፤ የፈለገውን ያህል አብዮታዊ በአድሃሪያን ጥይት ቢወድቅም፤ ባጭሩ ማንኛውንም መስዋዕትነት ቢጠይቅምና ትግሉ የፈለገውን ጊዜ ቢፈጅም፤ አብዮታውያን ከሁሉም በላይ መተማመን ያለባቸው በሃያ ስምንቱ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብና በኢትዮጵያ ምድር ሃበት ላይ ነው። ከዚህ ዓይነቱ እምነት መዛነፍ የመጣ ዕለትና ተስፋችንን በውጭ ሃይሎች ላይ መጣል ያመጣን እለት የተኮላሸ አብዮትና በነጻነት ለዘለአለም ትኑር! የተበለችው አገራችን ተመልሳ ከባርነት ስር የምትወድቀበት ቀን እንደሚመጣ ማገዛችን እንደሆን መታወቅ አለበት።*

ሌላም - በዚሁ በመጋቢት 1969 ወር ተደርጎ ስለነበረው የመኢሶን ብሔራዊ ኮንፈረነስ ውሳኔዎች የገለጸውና - „ከመሶን ጠቅላይ ኮሚቴ ለመ ኢሶን ደጋፊዎች በሙሉ“ በሚል ርዕስ በግልጽ ደብዳቤ መልክ የወጣው የሰፊው ሕዝብ ድምጽ ቁጥር 55 (ግንቦት 9 ቀን 1969) እትም፤ የሚከተለውን የኮነፈረንሱን አቋም አሳውቆ እንደነበር ለማስታወስ የሚቻል ነው።

„በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች በአለም አቀፍ ደረጃ የሚተባበሩበትን ያህል አብዮቱን ሊደግፉት መነሳታቸው ይታያል። የኢትዮጵያ አብዮት ከአለም ተራማጅ፣ ሶሻሊስት አገሮችና ድርጅቶች የሚያገኘው ማንኛውም እርዳታ ለትግሉ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ እሙን ነው። ነገር ግን መኢሶን የውጭ እርዳታን በሚመለከት በኩል ሁለት ነገሮችን መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ ያምናል።

<u>አንደኛው</u> የውጭ አገር ድጋፍ የዚችን ኩሩና ታሪካዊ አገራችንን ብሔራዊ ክብርና ነጻነት የማይነካ፣ ራሷን ለመቻል የምታደረገውን ጥረት የሚያግዝ እንጂ የማያደናቅፍ እረዳታ መሆን አለበት።

<u>ሁለተኛ፣</u> ማንኛውም ሕዝብ በውጭ እርዳታ ላይ በመተማመን አብዮቱን እግቡ ለማድረስ እችላለሁ ብሎ ካሰበ እራሱን ማታለሉ ብቻ ሳይሆን፣ አብዮቱንም ብሔራዊ ነጻነቱንም ያጣል። ማንም ሕዝብ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ኩሩና ባለታሪክ ሕዝብ ከሆነ ለገዛ ነጻነቱ፣ ለገዛ አብዮቱና ለገዛ ክብሩ ከሁሉም በፊት መተማመን ያለበት በራሱ መሆኑ መታወቅ አለበት። ስለሆነም የውጭ እርዳታን በሚመለከት በኩል ብሔራዊ ክብርና ነጻነት እንደዚሁም ከሁሉ በፊት በራስ መተማመን የሚለው መመሪያችን ይሆናል።“

ይህ ነው እንግዲህ፣ በወቅቱ በይፋ የተገለጸው አቋም። መኢሶን ሶቭየት ሕብረትን በሚመለከት ከዚህ በአደባባይ ከገለጸው ሌላ፣ ተናግሮም ሰርቶም አያውቅም።

## 6. መደምደሚያ

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ያተኮርነው፤ መሰረታዊ በሆኑት ዋና ዋና በሆኑት ጥያቄዎች ላይ ነው። አያይዘንም፤ በአንዳንድ አስተያየቶችና ተደጋግመው በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ ተመልሰናል። ወደፊት የምንመለስባቸው ጉዳዮች እንደሚኖሩም ለመገመት የሚቻል ነው።

ስለመኢሶን መኢሶን ስለራሱ፤ ከተናገረው ይበልጥም ሌሎች ብዙ ጽፈዋል። ብዙ በዙ ተናግረዋል። መኢሶን የኢትዮጵያ ሕዝቦች የስልጣን ባለቤት እንዲሆኑና ኢትዮጵያን በልጽጋ ከማየት በስተቀር፤ ሌላ ምኞትና ፍላጎት ያልነበረውና የሌለው ድረጅት ነው።

መኢሶን ባለው ሃይልና ችሎታ ከአብዮቱ ትግል ውስጥ በመግባቱ፤ ለአብዮቱ መራመድ አስተዋጽኦ አድረጓል። በኢትዮጵያ የፊውዳሊዝም መደምሰስ በየትኛውም መመዘኛ ቢሆን፤ አንድ ትልቅ የታሪክ እርምጃ ነው።

የመኢሶን መስመር፤ አሰራሩና ድርጊቱ ለአባለቱና ለወዳጆቹ ግልጽ የነበሩና ይፋ ውይይት የሚደረግባቸው በመሆናቸው፤ የድርጅቱን ውስጠዊ ዴሞክራሲያዊ ሕይወት ለመጠበቅና ለመንከባከብ ተችሏል። ስለሆነም በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ እንደደረሰው ሁሉ፤ በመኢሶን ውስጥ የርስ በረስ መገዳደልና መጠፋፋት አልደረሰም። ይህ የመኢሶን አዎንታዊ ገጽታ ነው። መኢሶን ከሌሎቹ ድረጅቶች የሚለየውና አይነተኛ የሚያደረገው ባሕርይ ምናልባትም ለውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሕይወትና ለምሁራዊ ውይይት ክፍት መሆኑ ነው ብለን እናምናለን። ይሁን እንጂ የመኢሶንን መጠቃት ያስከተለው በመሰረቱ የአብዮቱ መሸነፍ ቢሆንም፤

ድርጅቱን ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ያልተለዩት ለዘብተኝነትና ዳተኝነት ዝቅተኛ የማይባል አስተዋጽኦ እንደነበራቸው የማይካድ ነው።

በዚህ ጽሁፍ መቅድም ውስጥ እንደተገለጸው፤ መኢሶን የፖለቲካ ጉዞ ታሪኩን በሰፊ ጥናትና ምርምር ለማጤን ጥሯል። ከዚህም በተጨማሪ፤ ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በተገናዘበ፤ የፖለቲካ ፕሮግራሙን አሻሽሏል። ለትግሉ አላማ ለዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መመስረት መሆኑን ገልጿል። ይህም በዴሞክራሲያዊ ሕገመንግስት መሰረት የብዙ ፓርቲዎች ዲሞክራሲያዊ ሥርአት ማለት ነው።

መኢሶን እንደዚሁም <u>ዛሬ</u> ባለው የሃይሎች አሰላልፍና ሚዛን፤ አንድም አገር-አቀፍ ወይንም የብሔር ድርጅት ለብቻው የመንግስቱን አገዛዝ ገርስሶና ብቸኛ የስልጣን ባለቤት ሆኖ፤ በመላ ኢትዮጵያ ሰላምንና ዴሞክራሲን ሊያሰፍን የሚችልበት ሁኔታ አለ ብሎ አያምንም። የመኢሶን እምነት፤ የተለያዩት የመንግስቱ አገዛዝ ተቃዋሚ ሃይሎች ወደ አንድ ሰፊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር መምጣት አለባቸው የሚል ነው።

ይህ መሰረታዊ ጉዳይ እስካሁን ድረስ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተቻለ መሆኑ፤ ጉዳዩን ከትግለ አጀንዳ ላይ እንዲነሳ የሚያደርግ አይደለም። መኢሶን ስለዚህም፤ ሰፊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር እንዲመሰረት በሚያደርገው ጥሪና ትግል ይቀጥላል። በዚህም መንፈስ፤ ለውይይት መነሻ የሚያገለግል የገራ ሽግግር ፕሮግራም አቅርቧል።

በሥልጣን ላይ ያለው ወታደራዊ አገዛዝ ተቃዋሚ ድርጅቶች ብዙ ነን። መላው የኢትዮጵያ ሕዝቦች የአገዛዙ ተቃዋሚ ነን። በታሪክ ቁስሎች ተራርቀንና በጥርጣሬዎች

ታቅበን እስካለን ድረስ ግን፣ የምንመቸው ለመንግስቱና ለአገዛዙ መሰንበት ነው።

የኢትዮጵያ ተራማጆች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች ይህንን አጥር ለመስበር መብቃት ይኖርብናል። ለዚህ ካልበቃን፣ መጭው ትውልድና ታሪክ የሚከሱት መንግስቱ ሃይለማርያምን ብቻ አይሆንም። እያንዳንዱን ድርጅት እያንዳንዱን ግንባር፣ እያንዳንዱን ተራማጅ፣ እያንዳንዱን አገር ወዳድ ግለሰበ ሁሉ ነው።

መኢሶን ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ፊት የገባውን ቃል ለመጠበቅ በቆራጥነት የታገለ ድርጅት ነው። ሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ ነጻነት፣ እኩልነትና ፍትህ የሚጠይቁትን መስዋዕትነትን ለመክፈል፣ ምንጊዜም ሆነ በምንም ሁኔታ ወደሁዋላ ያላለ ድርጅት ነው።

በዚሁ መንፈስ አሁንም፣ ለሰላም፣ ለዲሞክራሲ፣ ለነጻነት፣ ለብሔሮች መብት መከበር፣ ለማሕበራዊ ፍትህና ብልጽግና በሚደረገው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ውስጥ አስተዋጽኦን ለማበርከት ዝግጁ ነው። በዚህም አኳያ፣ ከትግል ተሳትፎው የቀሰማቸው ትምህርቶች እንደሚጠቅሙት ይተማመናል።